DSpace Institution

DSpace Repository **http://dspace.org**

þÿ G e ½ e z Thesis

2018-06

þÿ è > p í è c õ ’ u ¥“ p c ` - u • p “

þÿ ` p (! è ¥ Ý = M u

þÿ ˜ , @ è

http://ir.bdu.edu.et/handle/123456789/17696

Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository



ባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ

ሂውማኒቲስ ፋኩሊቲ

የግእዝ ትምህርትክፍል

የሾተላይ የባሕል መድኃኒት እና አተገባበር ትንተና በተመረጡ የግእዝ መጽሐፈት

በ

አገኘሁ ፀጋየ ፈንቴ

ሰኔ 2018 ዓ/ም

ባሕር ዳር ኢትዮጵያ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

የግእዝ ትምህርት ክፍል

የሾተላይ የባሕል መድኃኒት እና አተገባበር ትንተና በተመረጡ የግእዝ መጽሐፈት መነሻነት።

የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ በግእዝ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

በ

አገኘሁ ፀጋየ

አማካሪ ዳዊት ዲበ ኩሉ (ፒኤችዲ)

ሰኔ፣2018ዓ.ም

ባሕር ዳር ኢትዮጵያ

ማረጋገጫ

የሶተላይ የባሕል መድኃኒት እና አተገባበር ትንተና በተመረጡ የግእዝ መጽሐፈት መነሻነት በሚል ርእስ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ሂውማኒቲስ ፋኩልቲ፣ በግእዝ ቋንቋና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለአርትስ ማስተርስ ዲግሪ በግእዝ ቋንቋና ስነ ጽሑፍ ለማግኘት እንደ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሠራ የራሴ ወጥ ሥራ መኾኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዬ የኾኑና ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ሕጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መኾኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡- አገኘሁ ፀጋየ ፊርማ፡- _____ ቀን፡- ----------/2018 ዓ.ም

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስ ፋኩልቲ

የግእዝ ትምህርት ክፍል

የመመረቂያ ጽሑፉ ለተቋቁሞ ብቁ መኾኑን ማረጋገጫ

በእኔ አማካሪነት በአገኘሁ ፀጋየ የተዘጋጀውን በሾተላይ የባሕል መድኃኒት እና አተገባበር ትንተና በተመረጡ የግእዝ መጽሐፋት መነሻነት በሚል ርእስ የተዘጋጀውን ይህን የመመረቂያ ጽሑፍ ክትትል ማድረጌን፣

ማንበቤንና መገምገሜን አረጋግጣለኹ፡፡ ይህ የመመረቂያ ጽሑፍ ለተቋቁሞ እንዲቀርብየይኹንታ ሐሳቤን አቀርባለኹ፡

…….. …… ……/……/……

የአማካሪ ስም ፊርማ ቀን

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስ ፋኩልቲ

የትምህርት ክፍል

የመመረቂያ ጽሑፍ ተቋቁሞ ውጤት ማረጋገጫ እንደ ፊተና ቦርድ አባላት ይህን የሾተላይ የባሕል መድኃኒት እና አተገባበር ትንተና በተመረጡ የግእዝ መጽሐፊት መነሻነት በሚል ርእስ በአገኘሁ ፀጋየ የቀረበውን የመመረቂያ ጽሑፍ ፈትነናል፡፡ ይህ የመመረቂያ ጽሑፍ

“የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ በግእዝ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ” ለማግኘት የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን

በማሟላቱ ተቀባይነት ማግኘቱን እናረጋግጣለን፡፡የፊተና ቦርድ አባላት

የውጭ ፈታኝ ስም----------ፊርማ----------ቀን----------

የውስጥ ፈታኝ ስም----------ፊርማ----------ቀን----------

የሊቀ መንበር ስም----------ፊርማ----------ቀን ----------

ምስጋና

ከኹሉ አስቀድሜ ከዚህ ላደረሰኝ የኹሉ ጌታና ባለቤት ለኾነው ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና አቀርባለኹ፡፡በመጀመሪያ ይንን ትምህርት እንድማር ለአደረጉኝ ለበተሰቦቼ ምስጋና ይግባቸው፡፡ በመቀጠልም ጥናቱ ከዚህ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ተገቢዉን እገዛና ምክር በመስጠት ለረዳኝ ለአማካሪዬ ለዳዊት ዲበኩለ(ፒኤችዲ) ምስጋናዬን አቀርባለኹ፡፡ እንዲሁም ለሥራዉ ውጤት እዚህ ላይ መድረስ በቁሳቁስም ኾነ በሐሳብ ለረዱኝ መምህሮቼ እና ጓደኞቼ ኹሉ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ በመጨረሻም ጊዜዬን በአግባቡ በመጠቀም ሥራዬን እንድሠራ አይዞኽ በማለት እና ሞራል በመስጠት ከጎኔ ለነበረች ውድ ባለቤቴ ክብርና ምስጋና ይድረሳት።

አጠቃሎ

ይህ ጥናት የሾተላይ የባሕል መድኃኒት እና አተገባበር ትንተና በተመረጡ የግእዝ መጽሐፈት መነሻነት በሚል ርእስ የቀረበ ነው። የምርምሩ ዋና ዓላማ ለሾተላይ መድኃኒት የሚሆኑ የባህል መድኃኒቶችን መርመሮ መተንተን ነው። የሾተላይ የባህል መድኃኒት አተገባበር እና የሕመሙ ዓይነት ፣ የፅፀዋቱ አገልግሎት ምን ይመስላል ? ባህላዊ መድኃኒት ለዘመናዊ መድኃኒት ምን አይነት አስተዋጽዖ አበርክቷል፣ አኹንስ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል ? የሚሉትን ይዘቶች በተመረጡ የግእዝ መጽሐፍት አንጻር ለመፈተሽ የታለመ ነው። የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት በእርግዝና ወቅት ደሙ እንዳይረጋና ቢጸነስም እንኮ ጽንሱ በሆዳቻው ላይ እንዳይቀመጥ ደሙ እንዲወርድ እያደረገ ብዙውን ጊዜ ይህ ነው ሊባሉ የማይችሉ እናቶች ሲቸጋገሩ ስላየሁ ነው።ስለዚህ ለእንደ እነዚህ ላሉ እናቶች መፍትሄ ለመፈለግ ነው።የጥናቱ መረጃም በዋናነት በሰነድ ፍተሻ ተሰብስቧል። ምርምሩም በዓይነታዊ ማለትም ከቁጥር ይልቅ ጽንሰ ሀሳብን በመተንተን የሚያቀርብ ከምርመር ዘውግ የሚመደብ ሲኾን መረጃውም በገላጭ ዘዴ ተተንትኖ ቀርቧል። ለዘመናዊ ሕክምና መሠረቱ ባህላዊ ሕክምና ወይም ባህላዊ መድኃኒት መኾኑ በጥናቱ ተረጋግጧል።ይህ ማለትም ሁለቱንንም ስናይ በብዙ ዘመናት ቀድሞ በመምጣት ባህላዊ መድኃኒት ሲያገለግል ቆይቶል።አኹን ላይ ዘመናዊ መድኃኒት በመስፋፋቱ በህላዊ መድኃኒት እየተረሳ መምጣቱን ጥናቱ ይጠቁማል። የሾተላይ በሽታ ምንነት፣መድኃኒቶቹ እና ገቢራቸው በቅደም ተከተል ቀርበዋል። በአምስቱም መጽሐፍት ውስጥ የሚገኙ የፅፀዋቶቹ ብዛት እና አገልግሎት እንዲሁም መገኛ ሥፍራዎች እና የሚሰጡት ጥቅሞችም የተገለጹ ሲኾን የሕመሙ ዓይነት ፣ መድኃኒቶቹና መገኛ ቦታቸውን ፣ ለህመሙ የሚሰጡትን ፈውስ እና ገቢራቸውን ጥናቱ አሳይቷል። መድኃኒቶቹም በሚበላ፣አንገት ላይ በሚንተላተል፣በክታብ መልክ፣ በሚዋጥ፣በሚጠጣ፣በሚታሰር መልኩ እየተመጠኑ የሚሰጡ መኾኑን ጥናቱ አረጋግጧል።በመጨረሻም ባህላዊ መድኃኒት ለዘመናዊ መድኃኒት መነሻ እንደ መሆኑ መጠን የመድኃኒት ፅፀዋት የሚመረቱበተን ቦታ በየወረዳው ለእያንዳንዱ ለባህህል ሐኪሞች እንኮ ባይሆን በአንድ ላይ አድርጎ የሚሰጥበትን ሁኔታ መመቻቸት እና ለተጨማሪ ጥናት መነቃቃትን ሊፈጥር እንደሚችል ተመላክቷል።

አጎጽሮተ ቃላት

ከዚህ በታች የቀረቡት ምጎጻረ ቃላት በጥናቱ ውስጥ ለአገልግሎት ውለዋል፡፡

ዘፍ. ኦሪት ዘፍጥረት

ዘፀ. ኦሪት ዘፀአት

ዋኢማ. ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል

አ. አንቀጽ

ቅ. ቅጠል

ዕዳ. ዕፀ ዳብዳቤ

ዓ.ም ዓመተ ምሕረት

ተ.ቁ ተራ ቁጥር

IES. Institute of Ethiopian Studies

BMO. British manuscripit Original

WHO. World Health Organaztion

f. folio

r. recto

v. verso

የቁልፍ ቃላት መፍቻ

መድኃኒት ማለት ሥር ምሶ፣ ቅጠል በጥሶ፣ የሚቀምሙት፣የራስ ምታት፣የሆድ ቁርጠት፣ የቁርጥማት፣ የውጋት፣ ማንኛውንም በሽታ የሚያድንና የሚገድል።

መንፈስ የማይጨበጥ፣ የማይዳሰስ እና የማይታይ ረቀቅ ነገር መንፈስ

ጠንቋይ መናፍስትን በመጥራት፣ በድግምት፣ በአስማት እና በመተት የሰውን ኹኔታ ወይም አንድን ነገር ለመለወጥ፤ የሚመጠውን ለመግለጥ የሚሠራ ሰው።

ገቢር ድርጊት፣ ተግባር፣ የአንድ ነገር ቅደም ተከተል ወይም ሂደት፤ የአደራረግ እና የአፈጻጸም ሥርዓት

ማውጫ

ርዕስ ገጽ

አጠቃለሞ vii

የቁልፍ ቃላት መፍቻ ix

1. መግቢያ 1

1. 1 የጥናቱ ዳራ 1

1.2. የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት 4

1.3. የጥናቱ ጥያቄዎች 4

1.4. የጥናቱ ዓላማዎች 4

1.4.1. ዋና ዓላማ 4

1.4.2. ዝርዝር ዓላማዎች 5

1.5.የጥናቱ ጠቀሜታ 5

1.6. የጥናቱ ወሰን 5

1.7 የጥናቱ አደረጃጀት 6

ምዕራፍ፡ኹለት የቀድሞ ጥናቶች ግኝት (Literactur Review) 7

2.የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት 7

2.1. ባህላዊ መድኃኒት መድኃኒት ምንድ ነው? 7

2.2.ባህል 9

2.3.የባሕል መዳኃኒት በኢትዮጵያ በማእዝ መጽሐፍት ላይ የተደረጉ ጥናቶችና የእኔ ምርምር የሚያስተካክለው ክፍተት 9

2.4.ባህላዊ መድኃኒት ለዘመናዊው መድኃኒት ያለው አስተዋፅየ 10

2.5.ባህላዊ መድኃኒት አሁን ላይ ያለው ሁኔታ 11

2.6.የሾታላይ በሽታ የመመርመሬ ዘዴ፣የዕፅዋት አቆራረትና አሰጣት መጠን 12

2.6.1መግቢያ 12

2.7.የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት 15

ምዕራፍ፡ሦስት የአጠናን ዘዴ 22

3.1.የጥናቱ ዘዴ 22

3.2.የጥናቱ ዓይነት 22

3.3.የናሙና አመራረጥ ዘዴ 22
3.4.የመረጃ አመራረጥ ዘዴ 23
3.5.የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች 23
3.5.1 Primary sources: የቀደማይየመረጃምንጭ 24
3.5.2.የካልኣይ የመረጃ ምንጮች 26
3.6. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ 27
3.7. የግእዝ እና አማርኛ የመድኃኒት መጽሐፍት 27
3.8. የግእዝ እና አማርኛ የመድኃኒት የመጽሐፍቱ ውጫዊ እና ውስጣዊ ዝርዝር መግለጫዎች (Physical and Content Description of the Manuscript) 27
3.8 2 መጽሐፈ መድሐኒት (BMO, 828) 30
3.8.3 ዕፀ ዳብዳቤ 33
3.8.4 መጽሐፈአድኅኖት 35
3.8.5.መጽሐፈ ፈውስ 37
3.9.የምርምር ሥነ ምግባር 39
ምዕራፍ አራት፣የመረጃ ትንተና ግኝት ማብራሪያ 41
4.1 መግቢያ 41
4.2 የሕመም ዓይነት 41
4.3.የሾተላይ በሽታ ምንነት 41
4.4.የመድኃኒት አይነቶች፣የመድኃኒቱ የአዘገጃጀት ዘዴ እና አተገበባር ሁኔታ በተመረጡ የግእዝ መጽሐፍት 43
4.4.1. የመድኃኒት አይነቶች፣የአዘገጃጀት ዘዴ እና የመድኃኒቱ አተገባበር በመጽሐፈ መድኃኒት (IEES.2444) 43
4.4.2.የመድኃኒት አይነቶች፣የአዘገጃጀት ዘዴ እና የመድኃኒቱ አተገባበር በመጽሐፈ መድኃኒት (BMO.828) 44
4.4.3 የመድኃኒት አይነት፣የአዘገጃጀት ዘዴ እና የአተገባበር ሁኔታ በዕፀ ዳብዳቤ 50
4.4.4.የመድኃኒት አይነት ፣የአዘገጃጀት ዘዴ እና የአተገባበር ሁኔታ በመጽሐፈ አድኅኖት 51
4.4.5.የዕፅዋት አይነት፣የአዘገጃጀት ዘዴ እና የአተገባበር ሁኔታ በመጽሐፈ ፈውስ 52
4.5. ከመጽሐፍት የተገኙ መረጃዎች በሠንጠረዥ 52
4.6.ከቃለ መጠየቅ የተገኙ ሀሳቦች 95

4.7.በአምስት የግእዝ መጽሐፍት ውስጥ የተመዘገቡ የእፅዋት፣የእንስሳት ምርቶችና የንጥረ ነገሮች ዝርዝር እና የሾተላይ በሽታ ሕክምና። 96
4.7.1.ዘርጭ እምቧይ ሥር 97
4.7.2 አከርማ 98
4.7.3.ሞይደር 98
4.7.4 የጥጃ ጨንገር 99
4.7.5.የዳብዛ ሥር 99
4.7.6 ድንግጣ 100
4.7.7 እምባሬ 100
4.7.8.ተቀጽላ 102
4.7.9 ባቄላ 103
4.7.10 ኑግ 104
4.7.11.ቀረጽ/ቀረጥ/ 105
4.7.12 ጥዋ /ጽዋ/ 106
4.7.13.ሞጓ ብርሌ 107
4.7.14. እርግፍ ገፎ 107
4.7.15. የጅብ ምርኩዝ 108
4.7.16. ቀጋ 108
4.7.17. ወይን 109
4.7.18.እሬት 110
4.7.19. ማር 111
4.7.20.ላንቁሶ 112
4.7.21. የደጋ አባሎ 113
4.7.22. ዕፀ ደብተራ 113
4.7.23.ጥንጅት 114
4.7.24. የሴት ቀስት 114
4.7.25.አመጅ 115
4.7.26.ወይራ 115

4.7.27.ዕፀ መናሂ 116
4.7.28.ክትክታ 118
4.7.29.ቁልቆል 120
4.7.30.ችፍርግ 121
4.7.31. ጽፍሬና 121
4.7.31.ቋንዶ በርበሬ 121
4.7.32. የምድር እምቧይ 123
4.7.33. ውሾኝ 124
4.7.34 ጥቁርና ቀይ አውጥ 124
4.7.35 የመብረቅ ከሰል 126
4.7.36.ሐረግ ሬሳ 126
4.7.37. ፍየለፊጅ 129
4.11.38.ሳሊጥ 129
74.39.ጣዝማ 130
4.7.40. ነፁ ሽንኩርት 131
4.7.41.ጂባራ 132
4.7.42.የሰሌን ፍሬ 133
4.7.43. መሩዝ 134
4.7.44. አቱች 134
4.7.45.ቀይ ሽንኩርት 134
4.7.46.አልቲት 136
4.7.47.ከርቤ 136
4.7.48.ነፁ ዕጣን 138
4.7.49. ቀጠጥና 140
4.7.50.ቀበርቾ 140
4.7.51.አጋም 140
4.7.52. የባሕር ጤፍ 142

4.7.53.ሙፈጫጭላ 142
4.7.54 እስስት 142
4.7.55. የማርያም መቀነት/ዕፀ ልባዊት/ 143
4.7.56.ግዜዋ 144
4.7.57 ደበቀድ 145
4.7.58. አበተሬ 145
4.7.59 ለሚ 146
4.7.60.አህያ ጭራ 147
ምዕራፍ አምስት፣ ማጠቃለያ እና የይኹንታ ሐሳብ 147
5.1 ማጠቃለያ 147
5.2 የይኹንታ ሐሳብ 149
6. ዋቢ መጽሐፍት 151
አባሪ አንድ 154
ቃለ መጠይቅለባህል መድኃኒት አዋቂዎች የቀረቡ ቃለ መጠይቆች 154
1ኛ ቃለ መጠይቅ 154
አባሪ ኹለት 155
ቃለ መጠይቅ፡- ለዘመናዊ ሕክምና ባለሙያ 155
አባሪ ሦስት 156

ፎቶ ግራፍ 1 የመጽሐፉ መድኃኒት ስዕል/lES 2444፣f.109v እና f.119r-120v.....21
ፎቶግራፍ 2 መጽሐፈ መድሐኒት/የመድኃኒት መጽሐፍ ብሪቲሽ 828/አንቀጽ 59/.....24
ፎቶ ግራፍ 3፣ዕፀ ዳብዳቤ.....26
ፎቶ ግራፍ 4፣የመጽሐፈ አድኅኖት መጽሐፍ(2010 ገጽ102 የተወሰደ.....27
ፎቶ ግራፍ 5፣መጽሐፈ ፈውስ/የድህነትመጽሐፍ/ETHIOPIEN 402 GURIAULE 98/መጽሐፍ 29
ፎቶ ግራፍ 6፡-ዘርፉ እምቧይ በአጥኚው በ2018ዓ/ም የተነሳ.....77
ፎቶ ግራፍ 7፣የሞይደር ምሥል ማሳያ.....79
ፎቶ ግራፍ 8 የድንግጣ ምሥል.....80
ፎቶ ግራፍ 9 የአምባጮ ምሥል.....80
ፎቶ ግራፍ 10 የተቀጽላ ምሥል.....82
ፎቶ ግራፍ 11 የባቄላ ምሥል.....83
ፎቶግራፍ 12 የኑግ ምሥል.....83
ፎቶ ግራፍ 13 የቀረጽ ምሥል.....86
ፎቶ ግራፍ 14 የጽዋ ምሥል.....86
ፎቶ ግራፍ 15፣የቀጋ ምሥል ማሳያ.....87
ፎቶ ግራፍ 16 የወይን ምሥል.....88
ፎቶ ግራፍ 17 የእሬት ምሥል ማሳያ.....89
ፎቶ ግራፍ 18 የማር ምሥል.....90
ፎቶ ግራፍ 19፣የደጋ አባሎ ምሥል ማሳያ.....91
ፎቶግራፍ 20፣እፀ ደብተራ ምሥል ማሳያ.....92
ፎቶግራፍ 21፣የሴት ቀስት ምሥል ማሳያ.....93
ፎቶ ግራፍ 22፣የዕፀ መናሒ ምሥል.....94
ፎቶግራፍ 23፣የክትክታ ማሳያ ምሥል.....96
ፎቶግራፍ 24፣ቁልቁልምሥልማሳያ.....98

ፎቶግራፍ 25፣የችፍርግ ምሥል ማሳያ 98
ፎቶግራፍ 26፣የምድር እምቦይ ምሥል ማሳያ 101
ፎቶግራፍ 27፣የአውጥ ዕፅዋት ምሥል ማሳያ 102
ግራፍ 28፣የሐረግሬሳንምሥልማሳያ 104
ፎቶ ግራፎ 29፣የጣዝማ ማር ምሥል 107
ፎቶ ግራፍ 30 የነጭ ሽንኩርት ማሳያ ምሥል 108
ፎቶ ግራፍ 31፣የጂባራ ምሥል 109
ፎቶ ግራፍ 32፣የአቱች ምሥል 110
ፎቶ ግራፍ 33 የቀይ ሽንኩርት ምሥል 111
ፎቶ ግራፍ 34፣የአልቲት ምሥል 112
ፎቶ ግራፍ 35 የከርቤ ምሥል 113
ፎቶግራፍ 36 በ2018 በአጥኚው የተነሣ ፎቶ 114
ፎቶ ግራፍ 37 የቀጠጥና ምሥል 116
ፎቶ ግራፍ 38 ፣የአጋም ተክልምሥል 116
ፎቶግራፍ 39፣የማርያም መቀነት/ዕፀ ልባዊት/ ምሥል 118
ፎቶግራፍ 40፣የግዜዋ ተክልና ፍሬ ምሥል ማሳያ 119

1. መግቢያ

1. 1 የጥናቱ ዳራ

የባህል መድኃኒት የሚለው ቃል ባህል እና መድኃኒት የሚሉትን ሹለት ጥምር ቃላትን የያዘ ሲሆን ትርጉሙ ሰዎች ሀገረሰባዊ ዕውቀትን ተጠቅመው በሽታን ለመከላከል እና ለመቋቋም ሲባል ከተለያዩ ዕፅዋቶች፣እንስሳት፣ ከተለያዩ ማዕድናት የሚያዘጋጁት መድኃኒት ማለት ነው።

"ባህላዊ መድሃኒት፣ ከተለያዩ ተፈጥሯዊ ነገሮች ማለትም ከዕፅዋት፣ ከእንስሳትና ከማዕድናት የሚዘጋጁ የተለያዩ ባህላዊ መድሃኒቶችን የሚያጠቃልል ዘርፍ ነው። በተጨማሪም ባህላዊ መድሃኒት መንፈሳዊ ህክምናን፣ የእጅ ህክምና ስልቶችን፣ በሽታን ለመከላከልና ጤንነትን ለመጠበቅ በግለሰብ ደረጃ ሆነ በቡድን የሚደረጉ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን፣ ለህመምተኛ የሚደረጉ እንክብካቤዎችንና ድጋፎችን፣ አካላዊ ምርመራዎችን፣ ህመምን ለመከላከል የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ሁሉ ያጠቃልላል።"(ሀብታሙ አቅናው 2018፣113)። ከዚህ የምንረዳው ሰዎች በቀላሉ ገንዘብ ሳያወጡ ያላቸውን እምቅ ዕውቀትን ተጠቅመው ጥንቃቄ በጠመላ መልኩ ለህመምተኛው ከአካባቢያቸው ከሚገኙ ከዕፅዋት፣ከእንስሳት፣ከማዕድናት በማዘጋጀት በባህል መልክ ስለሚሰጥ ነው።

የባህል መድኃኒት በኢትዮጵያ የተወሰነ ሰው ብቻ የሚጠቀመው የጥቂቶች ሀብት ብቻ አለመኾኑን ስለባህል መድኃኒት አዘገጃጀት፣አሰጣጥ እና አጠቃቀም በሚል ጥናታዊ ጽሑፉ ሲገልጽ ባህላዊ መድኃኒት የአንድ አገር ወይም የተወሰነ ጎብረተሰብ ክፍል የሚጠቀሙበት አይደለም።(ምህረት፣2000)።ይህ ማለት በሀገራችን በሁሉም አካባቢዎች ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬድረስ ለማኅበረሰቡ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ እና ሰው የሆነ ሁሉ ማንኛውም ህማም ሲሳማው ሀብታም ድሃ ሳይሉ በአኩል የሚጠቀሙት የጋራ ሃብት ነው።

‹‹ባህላዊ መድኃኒት ማለት በሽታን ለማከም ወይም ለመከላከል ተብሎ በጎብረተሰቡ ጥቅም ላይ የሚውል በባህላዊ መንገድ በዕፀዋት፣ በእንስሳት አካል እና ከማዕድናት የሚዘጋጁ መድኃኒቶችን የሚያጠቃልል ነው፡፡››(የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን፣ 2012፣5)፡፡በማለት ገልጿታል።

Traditional medicine is defined by the World Health Organization (WHO) (2015) as a teaching which incorporates different health improvements, approaches, knowledge, and beliefs, joining plant, animal, and/or mineral-based medications, spiritual therapies, manual methods, and exercises connected uniquely or in combination to maintainhealth as well as treat, analyze, or prevent illness.
"በዓለም ጤና ድርጅት (WHO) (2015) መሠረት፣ “ባህላዊ መድኃኒት” የተለያዩ የጤና ማሻሻያ መንገዶች፣ አተገባበሮች፣ እውቀቶችና ሀሳቦችን የሚያካትት፣ የዕፅዋት፣ የእንስሳት፣ ወይም የማዕድናት መድሃኒቶችን ከመንፈሳዊ ህክምና፣ ከእጅ ሥራ ዘዴዎች እና ከእንቅስቃሴ ስልጠናዎች ጋር በአንድነት ወይም በተለያዩ በመዋሃድ የጤና ጥበቃና ማሻሻያን፣ እንዲሁም በሽታን ለመፍታት፣ ለመተንተን ወይም ለመቀነስ የሚውል ትምህርት ነው።"

Yong (1970፣24) ገለጻ ደግሞ፣ "ባህላዊ መድኃኒት ስንል ዕፀዋትን፣ እንስሳትን፣ ማዕድናትን እና መንፈሳዊ የፈውስ ሥርዓቶችን መሠረት ያደረገ ነው በማለት ይናገራል።"

በመጨረሻም Sofowora (1982;2) የባህል ሕክምናን ወይም መድኃኒትን እንደሚከተለው ገልጸታል፡- "ባህላዊ ሕክምና ወይም መድኃኒት ማለት የዕውቀት እና የተግባር አጠቃላይ ድምር የሆነ አካላዊ፣ አእምሯዊ፣ ማኅበራዊና አካባቢያዊ ጠንቆችንና ተውሳኮችን ለመከላከል ለማስወገድና ለመመርመር ሲባል የሚተገበር በተግባራዊ ልምምድ እና ምልከታ የሚከወን ዕውቀቱና ጥበቡም በአብዛኛው ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል ወይም በጽሑፍ እንደሚተላለፍ ጠቁሟል። "

ባህላዊ መድኃኒት ታሪክ ከሚያስታውስበት ጊዜ ጀምሮ በተወሰኑ የዓለም ሀገራት አገልግሎ የሰጠ እና ዛሬም እየሰጠ ያለ የዕውቀት ዘርፍ ነው። የባህል መድኃኒት አጀማመርን አስመልክቶ"የሰው ልጅ በሽታን ለመከላከል መድኃኒት መጠቀም እና መፈወስ የጀመረው ከጥንተ-ክርስቶስ ልደት 5,000 ዓ.ዓ በፊት መኾኑን ዓለማየሁ (2000) ገልጿል።

ይህም ማለት የሰው ልጅ በምድራዊ ሕይወቱ ሲኖር በብዙ በሽታዎች ሊይያዝ እና ሊታመም ወይም ሊጓዳ ይችላል።ነገር ግን በሽታውን ተቋቁሞ ሕይወቱን ለማስቀጠልና ለታለመው አላማ ለማድረስ ወይም ውድ ሕይወቱን ለማቆየት ሲል ባህላዊ መድኃኒቱን መጠቀሙ የግድ ነው።የሀገራችን ማሕበረሰባችን ክፍል 80% አሁንም ቢሆን ባህላዊ ወይም

ሀገር በቀል መድኃኒቱን ተጠቃሚዎች ናቸው።"የሰው ልጅ ከ5000 ዓ.ዓ በፊት የበሽታን ሥቃይ ለማስታገስ መድኃኒት መጠቀምን እንደጀመረ መኮነን (1999፣ 29) ይናገራል፡፡" ባህላዊ መድኃኒት ሕክምና ዛሬም በገጠርም ኾነ በከተማ ያለው ኅብረተሰብ የጤና ችግር መፍቻ አድርጎ እየተጠቀሙት የሚገኝ የሕክምና ዘርፍ ነው።(ምሕረት፣2000)። ይህም ሲባል ሰዎች በኑሯቸው ለይ የሚያጋጥማቸውን ችግር እና የጤና ጉዳይ በባህላዊ መልኩ ሕክምናውን እያገኙ ይኖራሉ።

አኹን ላይ የሀገራችን የባህል መድኃኒት እና ሊቃውንት እንዲሁም ለባህል መድኃኒት የሚኾኑ ዕፀዋቶችን የመለየት እና የመመዝገብ ሥራ በኢትዮጵያ የምግብ መድኃኒት እና ጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ አዋጅ በማውጣት መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ መደረጉ ለባህላዊ መድኃኒት የተሰጠውን ትኩረት ያሳያል በማለት (ገብረ ሕይወት፣2014፣) ሀሳብን በጥናታቸው ለይ አብረርተዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ የባህል መድኃኒት አጀማመር በመጽሐፍ ቅዱስ በዋነኝነት ስለ መንፈሳዊ ሲያስተምር እግረ መንገዱን ብዙ ዓለማዊ ጉዳዮችን ይደስሳል።ከእነዚህ ውስጥ አንዱ መድኃኒት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ በቅድሚ ተመዝግቦ የሚገኝ ከግብፅ ውስጥ የሞተው የያእቆብ አስክሬን እንዳይበሰብስ ሥራ ለይ የወለው የአስክሬን ማድረቂያ መድኃኒት ነው።ነቢየ እግዚአብሔር ሙሴ ሕዝበ እስራኤልን እየመራ ማራ ወደሚባል ቦታ በደረሰጊዜ ውሃው መርዛማና መራራ ስለነበረ ሕዝቡና እንስሳቱ መጠጣት አልቻሉም በዚህ ሁኔታ ያዘነው ሙሴ ወደ እግዚአብሔር በጸለየ ጊዜ ዕፁን አሳየው። ዕፁንም ወስዶ ከውሃው ለይ አኖረበት ውሃውም ታከመና ሕዝቡና እንስሳቱ ጠጡ።ሐብታሙ አቃናው(2018፣)፤እንደገለጸው፡-ባህላዊ የዕፅዋት መድኃኒት ከተለያዩ የዕፅዋት ተዋጽያዎች የሚዘጋጅ፣ የሰው ልጅ ጤንነቱን ለመጠበቅ፣ በሽታን ለመከላከል፣ ከህመም ለመፈወስ፣ አካላዊ፣ አዕምሯዊና ስነ-ልቦናዊ በሽታዎችን ለማስወገድ ሲል የሚተገብራቸው የሰው ልጅ ከአጋጠመው የሥጋ ደዌ በባህላዊ መልኩ ምርመራ በመድረግ ከበሽታው የሚፈወስበት የመድኃኒት ዓይነት መኾኑን እንረዳለን።

ስለኾነም ሀገራችን ኢትዮጵያ ብዙ ዓይነት የባህል መድኃኒትወይምሀገር በቀል መድኃኒት ባለቤት እንደ መሆኖ መጠን ለብዙ የበሽታአይነቶች የባህል ሕክምናን እየሰጠች ትገኛለች። ከእነዚህ የባህል መድኃኒቶች ዋነኛውና አንዱ ደግሞ የሾተላይ የባህላል መድኃኒት ነው።

1.2. የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት

ይህንን ርእስ የመረጥኩበት ዋናው አነሣሽ ምክንያት ተወልጄ ባደኩበት ማለትም በአዊ ዞን በዳንግላ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ብዙ እናቶች ባል አግብተው ልጅ ወልደው የልጆቻቸውን ፍሬ ለማየት ይጓጓለ። ይሁን እንጂ በእርግዝና ወቅት ደሙ እንዳይረጋና ቢጸነስም እንኮ ጽንሱ በሆዳቻው ላይ እንዳይቀመጥ ደሙ እንዲወርድ እያደረገ ብዙውን ጊዜ ይህ ነው ሊባሉ የማይችሉ እናቶች ሲቸጋገሩ አያለሁ።ስለዚህ ለእንደ እነዚህ ላሉ እናቶች መፍትሄ ለመፈለግ ነው።

ኹለተኛ ደግሞ ከዚህ ቀደም የማውቃቸውን የባህል መድኃኒቶች ወደፊት በተግባር ሥራ ላይ ለማዋል ከሚታወቁ የባህል መድኃኒት ዐዋቂዎች ማለትም በጥበቡ የተካኑ የቤተክርስቲያን ምሁራን እና ግለሰቦች ላይ ዕውቀት ለመቅሰም ካለኝ ፍላጐት የተነሣ ሲኾን በሌላ መንገድ ሲታይ ደግሞ በባህላዊ መድኃኒት ዙሪያ የተወሰነ ግንዛቤ ያለኝ በመኾኑ በርእሰ ጉዳይ ዙሪያ የተለያዩ ጥናቶችን ሳነብ በሾተላይ ከዚህ ግባ ሊባል የሚችል ጥናት አለመደረጉ ነው፡፡በሦስተኛ ደረጃ አማራ ክልል በተለይም በአዊ ዞን ዳንግላ ወረዳ የሾተላይ በሽታ ከኅብረተሰቡ ዘንድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ስለመጣ በሽታው አስጊ እና አሳሳቢ በመኾኑ የተነሳ በሽታውን ለመቀነስ ነው።

1.3. የጥናቱ ጥያቄዎች

- የሾተላይ የባህል መድኃኒት በተመረጡ የግእዝ መጽሐፍት ውስጥ እንዴት ይገለጻል?
- የሾተላይ መድኃኒት በተመረጡ የግእዝ መጽሐፍት ውስጥ እንዴት ይተገበራል?
- የሾተላይ መድኃኒት በሚቆረጥበጥ ጊዜ የሚከናወኑ ቅድመ ሁኔታዎች ምንምን ናቸው?

1.4. የጥናቱ ዓላማዎች

1.4.1. ዋና ዓላማ

- የሾተላይ የባሕል መድኃኒት አተገባበር በተመረጡ የግእዝ መጽሐፍት መነሻነት ትንተና መስጠት ነው።

1.4.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- የሾተላይ የባህል መድኃኒት በተመረጡ የግእዝ መጽሐፍት ውስጥ እንዴት እንደ ሚገለጽ ማመልከት፣
- የሾተላይ መድኃኒት በተመረጡ የግእዝ መጽሐፍት ውስጥ አተገባበሩን መተንተን፣
- የሾተላይ መድኃኒት በሚቆረጥበት ጊዜ የሚከናወኑ ቅድመ ሁኔታዎችን መግለጽ።

1.5.የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ተሰርቶ ሲጠናቀቅ የሚከተሉት ዋና ዋና ጠቀሜታዎች ይኖሩታል።

- ሰዎች ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ኢኮኖሚያቸውን በመቆጠብ በትንሽ ገንዘብ መድኃኒቱን እንዲያገኙ ለመድረግ ይረዳል።
- ያለጊዜው የሚከሰጠውን የጽንስ መጨንገፍ ለማስቀረት ያግዛል።
- ጎብረተሰቡ የመዳኃኒቱን ፍጡንነት እንዲያዉቁና በሰነድ መልክ ተሰንዶ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ ይረዳል።
- በባሕላዊ ሕክምና ዘንድ ያለውን የሰዎችን ክፋ አመለካከት ይቀርፈል።
- እምቅ ጥበብ ያላቸው ሰዎች ጥባባቸውን ለሚከተለው ትውልድ እንዲያስተላልፉ ያግዛል።
- የባህላዊ መድኃኒት ፈዋሽነትን ከዘመናዊ መድኃኒት አተገባበር ጋር በማስተሳሰር ከፈውሱ ተጠቃሚ ለማድረግ ጉልህ ሚና ይኖረዋል።
- ለሚመጣው ትውልድ ማለት ስለሾተላይም ሆነ ስሌላው ባህላዊ መድኃኒት ጥናትና ምርምር ለሚያደርግ ሁሉ ለመረጀነት ያገለግላል።

1.6. የጥናቱ ወሰን

በዚህ ጥናት የሚጠናው ርእሰ ጉዳይ ጊዜን፣ገንዘብንና አቅምን ተሳቢ በማድረግ ትኩረቱና ገደቡ የተወሰነ ነው።ከእርእሱ ጉዳይ አንፃር በግእዝና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የሚጠኑት ብዙ ዓይነት የበሽታ ዓይነቶች ቢኖሩም የእኔ ትኩረት ግን የሾተላይ በሽታ መድኃኒት በባህላዊ ሕክምና እና ትግበራው ለይ የተገደበ ነው።

1.7 የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት መግቢያና ማጠቃለያን ጨምሮ አምስት ምዕራፎችን አካቷል። እነዚህ ምዕራፎች በአምስት ጥቅል ማዕቀፍ ተደራጅተዉ የቀረቡ ሲሆን የመጀመሪያው ምዕራፍ፤ የጥናቱን መግቢያ እና ማስተዋወቂያ ክፍል በመሆኑ የጥናቱን አጠቃላይ መልክ፣ ትኩረት፣ መዋቅር እና ሂደት ይገልጻል። በዚህ ምዕራፍ ሥር፤ የጥናቱ ዳራ፣ አነሣሽ ምክንያት፣ ዓላማ፣ የምርምሩ ጥያቄዎች፣ፋይዳ፣ ወሰን እና አደረጃጀት ቀርበዋል። በምዕራፍ ሁለት የጥናቱ ክለሳ ድርሳናት የተካሄደበት ክፍል ሲሆን፤ ለምርምሩ መነሻ ደጋፊና መሠረት የሆኑ ጽንሰ ሐሳባዊ ዳራዎች እና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ተካተውበታል።ሌለው በምዕራፍ ሦስት የጥናቱ ዘዴ፣ የጥናቱ ዓይነት፣ የመረጃ ምንጭ፣ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችእና የጥናቱን መተንተኛ ዘዴ ሲይዝ፤ ምዕራፍ አራት ደግሞ መግቢያ፣የበሽታው ምንነት፣በተመረጡ በግእዝ መጽሐፍት የሚገኙ የዕፀዋት አይነቶች መድኃኒት እና ሥርዓተ ገቢር በዓይነት እና በይዘት ተለይተዉ በሰፊው ትንታኔ ተሰጥቷል። በመጨረሻም በምዕራፍ አምስት የጥናቱ ማጠቃለያ፣ የይኹንታ ሐሳብ፣ ዋቢዎች እና አባሪዎች በማካተት ጥናቱ ተጠናቋል።

ምዕራፍ፡ኹለት የቀድሞ ጥናቶች ግኝት (Literactur Review)

2.የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

2.1. ባህላዊ መድኃኒት መድኃኒት ምንድ ነው?

መድኃኒት አዳኝ በሥጋ በኩልም ኾነ በመንፈስ በኩል ከማንኛው ጉዳት የሚያድን እና የሚጠብቅ ነው።በማለት(የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣1989)ይገልጸዋል። መድኃኒት ቃሉ የግእዝ ሲኾን መነሻው ድኀነ ከሚለው ግስ የተገኘ ባእድ ከምዕላድ ነው።በተጨማሪም ድኀነ የሚለውን ቃል መድኃን፣ መምለጥ ከተያዙ በኋላ ወይም ሳይያዙ መቅረት፣ መትረፍ፣ አንዳይያዙ መኾን የሚል ብያኔ ይሰጠዋል።(ኪዳነ ወልድ 2005)።መድኃኒት የሚለዉ ቃል ዘመናዊ መድኃኒት ከመምጣጡ በፊት መጠሪያነቱ የሚያገለግለው ለባሕላዊ መዳኃኒት ሲኾን ዘመናዊ መዳኃኒት ከመጣ በኋላ ግን ከዘመናዊዉ ለመለየት ባሕላዊ የሚል ስያሜ ተሰጠው።(ሙሴ ፣2014፣)።በጥናቱ ገልጿል። በጥንት ጊዜ ሰዎች ከልዩ ልዩ ዕፅዋት መድኃኒት እየቀመሙ ከበሽታው ይፈውሱ ነበር።የክርስቶስ አዳኝነት ለሰው ሁሉ ስለኾነ ክርስቶስ የዓለም መዳኃኒት (አዳኝ)ይባላል።

ከለይ ከተጠቀሱት ሀሰብ የምንረዳው መድኃኒትና ህመም የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች እንደ መሆናቸው መጠን ህመም በበረታ ቁጥር ጠባቂ መድኃኒት እንደ ሚያስፈልግ፣ሰው የሆነ ሁሉ የመድኃኒት ጥገኛ መሆኑን ያስረደሉ። በተጨማሪም እንዳሁኑ ዘመናዊው ሳይመጣ ራሱን ከህመም ለመከላከል ሕይወቱን ለማቆየት ሲል ከዕፅዋት ጋር አቆራኝቶ እንደ ነበርና አሁን ከአምላኩ ጋራ በመሆን ወደ ዘመናውነት እንደ ተሸጋገረ ያስረዳል።

መድኃኒት በቤተ ክህነት ሰዎች ዘንድ ጥበብ በሚል የሚገለጽ ሲኾን መነሻ የሚያደርጉት ደግሞ የሰሎሞንን ጥበብ ነው፡፡ ሙሴ (2014) በጥናቱ ጠቁሟል። ዮሴፍም ባለመድኃኒቶች አገልገዮቹ አባቱን በሽቱ ያሹት ዘንድ አዘዘ፣ባለመድኃኒቶችም እስራኤልን በሽቱ አሹት።

ሙሴ ነብዩ(2014)፣መድኃኒት የሚለው ቃል ዘመናዊ መድኃኒት ከመምጣቱ በፊት መጠረያነቱ የሚያገለግለው ለባህላዊ መድኃኒት ሲኾን ዘመናዊ መድኃኒት ከመጣ በኋላ ግን ከዘመናዊው ለመለየት ባህላዊ የሚል ስያሜ ተሰጠው፡፡ ሐዲስ (1980፣ 48) "ባህላዊ እና ዘመናዊ መድኃኒት የሚዘጋጁት ከዕፀዋት፣ከእንስሳት እና ከማዕድናት መዘጋጀታቸው አንድ ቢያድርጋቸውም ተግባር ላይ ግን ባህላዊ እና ሳይንሳዊ ዘዴ መከተላቸው ልዩ

ያደርጋቸዋል ሲል ገልጿል።" ከዚህ በመነሣት በአኹኑ ጊዜ "መድኃኒት ባህላዊውን እና ዘመናዊውን ሲያጠቃልል ዘመናዊ መድኃኒት ከባህላዊ የሚለየው የተመጠነ እና ሳይንሳዊ በኾነ መንገድ ለሰው ከመሰጠቱ በፊት በእንስሳት ስለሚረጋገጥ እና የመድኃኒቱም መጠን ተመጥኖ በእድሜ ደረጃ በመከፋፈል ለሕፃናት እና ለዐዋቂ ተብሎ ስለሚከፈል ከባህላዊ መድኃኒት ልዩ ያደርገዋል በማለት ይገልጻል"(Hidan Yuan, 2016)።

ይህ ማለት ባህላዊውም ሆነ ዘመናዊው ሁለቱም የሚዘጋጁት ከተመሳሳይ ማለትም ከዕፅዋት፣ከእንስሳት እና ከማዕድናት ሲሆን ልዩነታቸው ግን መድኃኒቱን መጥኖ መስጠጥ ያለመስጠጥ ላይ ነው።ባህላዊው በመጀመሪያ በመመጠን ለህፃን ለአዋቂ በማለት በበቂ አባቶች በቀጥታ ይሰጣል።ነገር ግን ዘመናዊው ግን ለሰዎች ከመስጣት ይልቅ ከእንስሳት በመፈጠን ወደ ሰው ያመጣል።

ባህላዊ መድኃኒት ያለ ቤተ ሙከራ ቀጥታ ለሰው ስለሚሰጥ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል የሚል አስተሳሰብ በመኖሩ ባህላዊ የሚል ስያሜ የተሰጠው ይመስላል። ቢኾንም የአረቂ መለኪያ እንዳለው ኹሉ ለባህላዊ መድኃኒትም ሳይንሳዊ ባይኾንም በባህላዊ መንገድ መጥኖ የመስጠት እና በእድሜ ደረጃም ቢኾን ለዐዋቂ እና ለሕፃናት በማለት የተከፈለ ስለኾነ በዘፈቀደ የሚሰጥ አለመኾኑም መረሳት የለበትም።አያይዘውም (ሙሴ ነብዩ 2014)በማለት በጥናታቸው ላይ ጠቁመዋል።

የባህል መድኃኒት ባለሙያዎች በራሳቸው አረጋግጠው እና ብዙ ጥናት አድርገው ስለሚሰጡ አንደሚወረው አሉባልታ አይደለም በማለት (ሙሴ ነብየ 2014፣) በጥናታቸው ላይ ጠቁመዋል።ዴቪድ ወርነር (1994 ፣37) "አንዳንድ ዘመናዊ መድኃኒቶች ከነባሩ ባህላዊ የመድኃኒት ዘዴዎች ይሻላሉ። ዐልፎ ዐልፎ ግን የባህላዊ መድኃኒቶች ፍቱን ኾነው ይገኛሉ በማለት ገልጸታል። ስለዚህ ኹለቱም ጠቃሚዎች መኾናቸውን ያመለክታል።"

"መድኃኒት እንደዬ ሥራ ዘርፉ የተለያዬ አገላለጽ ሊሰጠው ቢችልም አካላዊ እና መንፈሳዊ ሕመምን፤ ችግርን፤ ሥቃይን፤ የሚያጠፋ፤ የሚያስታግስ፤ ለወደፊትም እንዳይከሰት የሚከላከል ኃይል ነው በማለት ገልጿል (መኮነን፣ 1999፣ 29)።"በአጠቃለይ መድኃኒት ከሥጋዊ የህመም ስሜት እንድንድንበት የተሰጠን የሰዉ ልጅ ትልቁ ሀብት መኾኑን እንረዳለን።

2.2.ባህል

ባህል ማለት ነገር፣ ክርክር፣ አባበል፣ የአነጋገር፣ የነገር ስልት፣ ትርጓሜ፣ምሥጢር፣ ድርሳን፣ ልማድ፣ ሕግ፣ ሥርዓት፣ የሃይማኖት ትምህርት፣ ቃል ድምጽ ነው።(ኪዳነ ወልድ 2005).

አማርኛ መዝገበ ቃላት(1989)ደግሞ ባህል ማለት የአንድ ኅብረተሰብ የአኗኗር ዘዴ፣ ወግ፣ ልማድ፣ እና እምነት በማለት ገልጿታል። "Tradition', Gr. !Apostolikh; paraVdosi") is the most important canonico-liturgical ancient Christian writing. (Encyclopaedia volume.4.p.980)."

"በሀገራችን አኹን ባለው ተጨባጪ ኹኔታ የባህል መድኃኒቶችን ጨምሮ ሌሎች ነባር ባህላዊ እሴቶች እየጠፉ እና እየተቀየሩ መኼዳቸውም የዚሁ ማስረጃ ው"። (ተዘራ፣ 2020)። ባህል ጠፋ ማለት ጥንታዊ ዕውቀቶችም አብረው ስለሚጠፉ ከእነዚህም አንዱ የባህል መድኃኒት አብሮ ይጠፋል ማለት ነው።

በአጠቃላይ ባህል ከማሕበረሰብ ከትውልድ ወደ ትውልድ በቅብብሎሽ የመጣ ሕግ፣ ሥርዓት፣ ደንብ፣ መመሪያ ማለት ነው። አንደ ዘመኑ ሰው ባልሰለጠነበት ወቅት በባህልእና ልማድ የእራሱን ሕግና ደንብ በመውጣት ሳይተራተር በእምነት በመቀበል ብቻ ይኖር የነበረ ተውፊት ነው።በመሆኑም ባህሉን ከአስቀጠልን ከጥንት ጀምረው ያሉ መድኃኒቶችም አብረው ይጠፋሉ።ስለዚህ ባህልና ሀገረሰባዊ ዕውቀት በአንድ ላይ የተያያዙ በመሆናቸው አንዱ ላንዱ የተያያዙ ናቸው።

2.3.የባሕል መዳኃኒት በኢትዮጵያ በግእዝ መጽሐፍት ላይ የተደረጉ ጥናቶችና የእኔ ምርምር የሚያስተካክለው ክፍተት

መኮነን(1999፣29)"በሀገር ደረጀ ስለባህል መድኃኒት ስንመለከት ኢትዮጵያም እንደቻይና ሞሶፖታሚያና ግብፅ ከጥንት ዘመን ጀምራ የባህላዊ መድኃኒትተ ጠቃሚ እንድኾነች" ገልጿታል።ይህ ማለት የሚያሳየን የኢትዮጵያ የባህል መድኃኒት አጠቃቀም ከጥንት ጀምሮ ሲካሄድ የቆየና አሁን ለሀገራችን ከፍተኛ አስተዋፅያ እያረገ የሚገኝ ነው።ከኢትዮጵያ ውጭም በሰለጠነው ዓለም ባህላዊ መድኃኒትን እንደ አማራጭ ይጠቀሙበት ነበር።

አንደ መሴ (2014) ገለጻ የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ መሠረቱ ባህላዊ መድኃኒት መኾኑን በግልጽ ያስረዳል። በመኾኑም የአኹኑ ትውልድ ይህን ጥንታዊ ዕውቀት የራሱ መኾኑን በመገንዘብ ቢጠብቀው እና ቢጠቀምበት፣ የራሱን ትቶ የሰው ፈላጊ ከመኾን ይልቅ የራሱን

በራሱ በማሳደግ እና ሌሎች የእኛን እንዲያውቁ በማድረግ ጥንታዊነቱን በጥናት በማረጋገጥ ለባእዳን ማሳወቅ ያስፈልጋል፡፡ስለዚህ የባህል እሴቶች እና የባህል መዳኃኒቶች እየጠፉ በሄዱ ቁጥር መድኃኒቱን ማወቅ ቀርቶ እየተዉነዉና እየረሳነው እንሄዳለን።

2.4.ባህላዊ መድኃኒት ለዘመናዊው መድኃኒት ያለው አስተዋፅዖ

ባህላዊ ሕክምና ለዘመናዊ ሕክምና መሠረት እደኾነ ነው የምንገነዘበው፡፡ ከዚህ በመነሣት ዘመናዊ ሕክምና የተቋቋመው በባህላዊ የሕክምና ዘዴዎች ላይ ሲኾን አኹን ግን ቀዳሚው የሕክምና ተግባር እየጠፉ ዘማናዊው ብቻ እየተስፋፉ ይገኛል፡፡ ምሕረት (2000) የገለጻውን ሙሴ (2014) በጥናቱ ተጠቅሟል።ለዚህ ወደ ዘመናዊነት የመሄድ አዝማሚያም የባህለዊ ሕክምናን ተንኳይ ፣ደብተራ በማለት በሀገር በቀል ዕውቀት የሚሠራዉን ሰዉ በማሸማቀቅ እንዲተው ማድረግ ነው።

ኬኬ(2012፣ 17) "ደግሞ "ቻይናውያን አኹን ዓለም ለደረሰበት ስልጣኔ መሠረቱና መነሻው የጥንቱ ስልጣኔ መኾኑን አጥብቀው ያምኑበታል" ሲል ገልጿል።የባህላዊ ሕክምና ጥቅም ከፍተኛ መኾኑ አያጠራጥርም፡፡ ነገር ግን ዝግጅቱ በበለጠ ተጠንቶ ያጠቃቀም ዘዴውም ተሻሽሎ በዘመናዊ መልክ ለሕዝቡ አገልግሎት ማቅረብ ይቻል ዘንድ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ይላል ሐዲስ (1980፣ 9)፡፡ የገለጸውን (ሙሴ 2014፣16) በጥናቱ ገልጿል። ግርማ መንግሥቴ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ (መጋቢት/18/2012) " ዘመናዊ ሕክምና ከመምጣቱ በፊት ባህላዊ ሕክምና መቶ በመቶ ሲያገለግል ዘመናዊ ሕክምናም ከመጣ በኋላም ሰማንያ ከመቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠቀመው የሕክምና ዘዴ ነው።

በማለት ስለባህላዊ የሕክምና ዘዴ የጻፈውን ያስረዳል"።በመቀጠልም ከዓለም ኃያላን ሀገሮች ውስጥ ጥንታዊ ግሪኮች፣ ግብፃውያን፣ አሦራውያን፣ ቻይናውያንና ሮማውያን የባህል ሕክምና ጠበብቶች እንደነበሯቸው እና የሚፈውሱበትም ባህላዊ የሕክምና መድኃኒት አንዱ ማር እደነበር (ኬኬ፣ 2007፣36) ፡ ያለውን ሀሳብ(ሙሴ 2014) በማንሳት በጥናቱ አቅርቧል።Chavunduk (1994; 10) "ዘመናዊ ሕክምና የማይፈውሳቸዉን በሽታዎች ያድናልና ባህላዊ መድኃኒት መቀጠል ይኖርበታል"ሲል ጽፏል፡፡ ምሕረት (2000፣ 8)" በዘመናዊ ሕክምና መፍትሔ ያልተገኘላቸዉ እንዳለ ጠቅሶ የሚከተሉትን እንደምሳሌ አቅርቧል፡፡ ለምሳሌ፡- ኪንታሮት፣ ነቀርሳ፣ ችፌ፣ አውድቅ እና ልፋ እንዲሁም ከመንፈስ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ በሽታዎች ዛር፣ ጂን፣ ክፉ ልክፍትና ዓይነ ጥላ ፈውስ የሚያገኙት

በባህላዊ መድኃኒት ነው" ሲል ያስረዳል፡፡ እውነት ነው የዘመኑ ጥበብ እስከ አኹን ድረስ ተመራምሮ ያልደረሰባቸዉ በሽታዎች መኖራቸዉ አያጠራጥርም፡፡ የዘመኑ ሐኪሞች ቢኾኑም የሚክዱት አይደለም፡፡ ከላይ የተጠቀሱት በሽታዎች ፈውስ የሚያገኙት በባህላዊ የሕክምና ዘዴ በመኾኑ ከሞላ ጐደል ዐልፎ ዐልፎ ጎብረተሰቡ አኹንም ድረስ ወደ ዘመናዊ ሕክምና መኸዱን ትቶ ባህላዊ መድኃኒት ማዘውተሩ ሙሉ በሙሉ እምነቱ በሀገረሰብ መድኃኒት ላይ የጠነከረ አቋም እንዳለዉ ያሳያል፡፡ ይህም ተግባር የሚያሳየው ባህላዊ መድኃኒት የሚሰጠው ፈውስ ቀላል አለመኾኑንእና በበሽታው ምክንያት በፊት ሁሉም ባለ መድኃኒትእንደ ነበረ አሁን ግን ዘመናዊውን ምክንያት በማድረግ ሰው እየተወ እና መድኃኒቱንም እየረሳነው መምጣቱን ያሳያል።

2.5.ባህላዊ መድኃኒት አሁን ላይ ያለው ሁኔታ

"ዓለም ለሃያ ሃንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ለደረሰችበት የሕክምናው ምጥቀት እና እድገት ሥር መሠረቱ የሚመዘዘው ከ3000 ዓመታት በፊት ካለው ጥንታዊ የሕክምና ጥበብ እነደኾነ ቻይናዉያን ጽፈዋል" ሲል ኬኬ (2012፣17) ይናገራል፡፡ በሀገራችን ኢትዮጵያ አሁን ለይ ባህላዊ መድኃኒትም የኾነ እሴት ቀንሶ የነበረ ቢኾንም እንደገና እያንሰራራ ይገኛል። ዴቢድ (1994፣ 3) "አብዛኛውን ጊዜ የሰዎች ባህላዊ ሕክምና እየጠፋ የመጠው ዘመናዊ የሕክምና ዘዴ እያደገ ከመጣ ወዲህ ነው" በማለት ገልጿል።ይህ ማለት ጥንታዊ የህክምና ጥበብ አሁን ባለንበት የእድገት መሠረት መሆኑንና ጃይናዊያንም አሁን በደረሱበት የእድገት ጎዳና ባህላዊ ህክምና መሆኑንaመሆኑን አጥብቀው ያምኑበታል።

ሀብታሙ (2018፣ 126) "እጅግ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸዉ የባህል መድኃኒቶች አኹን አኹን በማኅበረሰቡ ዘንድ መጠቀሙ እየቀረ እና በዚያው ልክ ደግሞ ሙያው ከትውልድ ወደ ትውልድ የመተላለፊያ መንገዱ አደጋ ውስጥ መኾኑን በግልጽ አቅርቧል"፡፡ ስለዚህ በኹለቱም አቅጣጫ የሀገር ሀብት መኾኑን በመረዳት የባለቤትነት ድርሻ የኹሉም ማኅበረሰብ ስለኾነ ልዩነቶች በውይይት በመቅረፍ ወደፊት ምሁራን በርካታ ምርምር በማድረግና ችግሩን ነቅሶ በማውጣት ወደ ነበረበት መመለስ ይቻላል፡፡(ሙሴ 2014)በጥናቱ ለይ አስቀሞቷል።ይህ ማለት ለመድኃኒትነት የሚውሉት ዕፅዋቶች በዘመናዊ ሰበብ በማስተጋት እና ለትውልዱ ባለመተላለፋቸው ብዙ ለመዳኃኒትነት የሚውሉት ዕፅዋቶች እየቀነሱ መጥጠዋል።፡

ባህለዊ መድኃኒት አሁን በሀገራችን በኢትዮጵያ የሚገኝበት ደረጃ ምን ይመስላል? በተለይም የቤተክርስቲያን ሊቃውንት በጥንቃቄ በቃል ኪዳን በተከታይ ጥንቁቅ ደቀመዛሙርት ሲያውርሱት የኖረው አገራዊ ወይም የባህል መዳኃኒት እና አስማት በአሁኑ ጊዜ ቸል የተባለ ይመስላል።ሙያውንም የሚያከናውነውን የቤተክርስቲያን ምሁር በራሱ ወገኖች ሳይቀር ጠንቆይ የመሸማቀቂያ ስለሚሰጠው እየተረሰ መጥቶል። መንግስትም በኩል ሲታይ በመስከም 23/1994ዓመተ ምህረት አዲስ ዘመን 6ኛ ዓመት ቁጥር 23 ገጽ 6 በዋኢማ ለባህል መድኃኒት አዋቂዎች ጥሪ ቢቀርብም በአሁኑ ሰዓት ግን ብዙም እየተሰራበት አይደለም።(ሙሴ፣2014)።ስለዚህ ከዚህ የምንረዳውበባህላዊ መድኃኒት የሚሰጠው ፈውስ ጥቁረት ቀላል አለመኾኑን ነው።

2.6.የሾታላይ በሽታ የመመርመሬ ዘዴ፣የዕፅዋት አቆራረትና አሰጣት መጠን

2.6.1መግቢያ

በባህላዊ ህክምና ተግባር ውስጥ፣ የሾተላይ የህመም ምርመራ ሂደት በታካሚው ሁኔታ በቀጥታ ጥያቄ መስጠት በመጀመሪያ ይጀምራል። ስለዝህ ባህላዊ ሐኪሞች ዘንድ በመጀመሪያ ደረጃ ዕፅዋትን ቆርጠው መድኃኒት ከመስተጣቸው በፊት የህመምተኞችን ጤንነት ማወቅ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው። በመከተለም የበሽታውን አይነት እና ሁኔታው ከታወቀ የዕፅዋት አቆራጥ እና መጠን እንደሚከተለው ይከናወናል።

ሀ.ምርመራ፡-የዚህ የበሽታ ህመም ምርመራ ታካሚውንጥያቄ በመጠየቅ እንዲህ በማለት ይጀምራል።“ምንዎን ነው የሚያምዎ?” ወይም“ ከጀመሮት ስኔት ወርሆ ነው? ”ያሉጥ ያቄዎችን ይጠይቃል። ሕመም ምርመራ ውስጥ የቆይታ ጊዜ ትልቅ አስፈላጊነት እንዳለው ይጠቅማል። ስለሆነም የዚህ አይነት የምርመራ ሂደት የእራሱ የሆነ አንድ ወጥ መለኪያ የለውም። በመሆኑም ታካሚዎች ትክክለኛውን ጊዜ በይገልጹም የበሽታ የቆይታ ጊዜን በባዓላት ቀንና ከወርሃዊ መታሰቢያቸው ጋር በመያያዝ በዚህ ወር በአምስት ቀን ፣በአሥር እንዲሁም በማርያም ዕለት፣ በባዓለ እግዚአብሔር ዕለት፣ በመጋቢት ወር፣ በሚያዚያ ወርበ ማለት የህመም የጊዜ ቆይታቸውን ይገልጻለ። መርመሪውም ከሰጡት ሀሰብ በመነሳት ከአለው የእውቀት ደረጃ ጋር በመገናዘብ ትክክለኛውን ህክምና ለመሥጠት ይጀምራል።

"የታመመን ሰው የጤና ችግር ለማወቅ በቅድሚያ ቁልፍ የኾኑ ጥያቄዎችን መጠየቅ እና በመቀጠልም ምርመራ ማድረግ አስፈላጊ መኾኑን ዴቪድ (1994፣ 73) ይገልጻል።"

የባህላዊ የመመርመሬ ዘዴ ሂዳት እንደ ዘመናዊ የሰለጠነ የተለያዬ መሣሪያዎችን ሳይጠቀም የቃል ጥያቄና የታመመውን አካል በመመልከት የሚመራመር ተግበር ነው። በባህላዊ ህክምና ባህላዊ በሽታን የመለያ ዘዴን ሐብታሙ(2018) በጥናታቸው ለይ ሲገልጹ የባህል መድሃኒት ዘርፈ ብዙና ውስብስብ ነው። ዘርፈ ብዙና ውስብስብ በመሆኑ ምክንያት ለተለያዩ አካላዊ፣ ስነልቦናዊ፣ አእምሯዊ፣ ማህበራዊ እና መሰል ውስብስብ ችግሮች ሊዳርግ ይችላል። ስለዚህ በባህል መድሃኒት ህክምና የመድሃኒቱን ምንነት ማወቅ ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱን የበሽታ ዓይነትና ለበሽታውም ተገቢ የሆነውን ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት ማንነት ለይቶ ማወቅን የሚጠይቅ ትልቅ ተግባር ነው።

እንደ Young(1970)፣ Konadu(2007)፣ ተመስገን(2003) እና Sofowora (1982፣26-28) ገለጻ "የተለመዱ የበሽታ መለያ ዘዴዎች የሚባሉት ዕይታዊ ምርመራ፣ ክሊኒካዊ ምርመራ ፣ ባዮሎጂካዊ ምርመራ እና ህመምተኛውን በአትኩሮት በመመልከት መለየት እንደሆኑ ይገልጻሉ።"

በአብዛኛውን ጊዜ የዚህ የሾተላይ በሽታ መመርመሪያ መንገዱ የተሰታቸውን ጥበብ በመጠቀም በጠልሰም፣በቃለ መጠየቅና ሴትዮዋ በምትሰጠው ሀሳብ በመነሳት ነው። ህመሙ እንዴት እና መቼ መቼ ነው የሚያምሽ?ተብላ ስትጠየቅ የህመሙ አይነት ብዙ ቢሆን ጽንሱ ከጀመረ ወር ወይም ኹለት ወር፣ወይ ደግሞ ከሦስት እስከትወልድ የለውን ጊዜ በመጥቀስ ያልረጋና የጓጓረ ደሞ መውጣት፣ጽንሱ ሳይቀር ደም ብቻ ኹኖ መውጣት ብላ ስትመልስ ከዚህ በመነሳት እና ከወለደችም በሆላ የተወለደው ህፃን የሚሞትበት ከሆነ በሽታ መኖሩን ማወቅ ይቻላል።ሌላው ደግሞ በዓይኖ ስታይ የሚያለክስ ከኾነ በዐይኖ አይታ የምትገድለው ከኾነ፣መጀመሪያ በሰለም ወልዳ በኹለተኛው ላይ እንደነዚህ አይነት ነገር የሚከሰትበት ከሆነ እና ሌሎችንም ምልክቶችን በመጠየቅ ምርመራ ይካሂዳለል።

ለ.የዕፀዋት አቆራረጥ፡-ባህላዊ ሃኪሞች ባህላዊ መድሃኒቱን በመሰብሰብና በማዘጋጀት ለበሽተኛው ለመስጠት በቅድሚያ ባህላዊ በሆነ መንገድ የበሽታውን ዓይነት ከለዩ በኋላ የባህላዊ መድሃኒት የዕፀዋት ግብዓቶችን ማሰባሰብ ይጀምራሉ።የባህል መድኃኒት ባለሙያዎች የመድኃኒት ዕፀዋትን በሚቆርጡበት ሰዓት ጸሎት የሚችሉት ከአንቀጸ ብርሃን ውስጥ አንቲ ውእቱ ዕፅ ቡሩክን እና ዕፀ አንግሥ በመድገም የሚፈለገውን ዕፀ ይቆርጣሉ። ለዚህም መሪራስ (2000) ዕፀዋት በሚቆረጡ ሰዓት የሚደገሙትን ጸሎቶች አስቀምጠታል።

አንቲ፡ውእቱ፡ ዕፅ፡ ቡሩክ፡ ዕፀ፡ ሕየወት፡ ዕፀ፡ መዳኃኒት፡ህይንተ፡ ዕፀ፡ ሕየወት፡ ዘውስተ፡ ገነት፡ ዘኮንኪ፡ ዕፀ፡ ሕየወት፡ በዲበ፡ ምድር፡ ፍሬኪኒ፡ ፍሬ፡ ሕይወት፡ ውእቱ፡ ወዘበለዐ፡ እምኔሁ፡ ሕይወተ፡ ዘለዓለም፡ የሐዩ፡ (ጸሎተ፡አንቀጸ፡ብርሃን) ።

"አንቺ የተባረክሽ ዕፅነሽ፤ የሕይወት እና የድኅነት ዕፅነሽ። አንቺ በገነት ውስጥ ያለው የሕይወት ዕፅ ፈንታ በዚህ ዓለም የሕይወት ዕፅሆነሽ ፍሬሽም የሕይወት ፍሬ ነው፤ ከእርሷ የበላ ሁሉ የዘላለም ሕይወትን ይኖራል።"(ከ«ጸሎተአንቀጸብርሃን»)

ሀብታሙ አቅናው (2018) ላይ በቃለመጠየቅ እንደረጋገጠው ለምሳሌ፣ መሪጌታ ስሙርና መሪጌታ ሕላዌ ለሾተላይ በሽታ የሚያገለግለውን ዕፅ ሲቆረጡ አጥኝው በአካል ተገኝቶ ክዋኔውን ለማየት እንደሞከረው ይህን የዕፅዋት መድሃኒት ለመቁረጥ ከሚያስፈልገው ቁስ ውስጥ የቀንድ ካራ/ ቢላዋ አንዱ ነው። የቀንድ ካራው ደግሞ እንዲሁ አገልግሎት ላይ አይውልም፡፡ ድምድም ኮስን ያለው አውራ ዶሮ ተይዞ መድሃኒቱ ያለበት ቦታ ወስደው የዕፅ አንግስ ጸሎት የሆነውን "የጸሐይና የጨረቃን ሹመት ሽሬ ላንቺ ሹሜሻለሁ። የእከሌን ልጅ አስወልጅ"፣ ብለው ሶስት ጊዜ ጸሎት ካደረሱ በኋላ በተያዘው የቀንድ ካራ/ቢላዋ የአውራ ዶሮውን ኮስን በቢላዋው/ በቀንድ ካራው በማድማትና ደም በማስነካት መድሃኒቱን ከሶስት ቦታ ቆፍረው በማውጣትና አሁንም ከደሮው ደም ስሮቹ ይነኩና ስሮቹን ባንድ ላይ በቀለበት መልክ ክብ ይሰሩና ውሃ ባልነካ ሃገሬ/ ፈትል ጨርቅ ተጠቅልሎ መድሃኒቱን ነብሰ ጡር ለሆነች ሾተላይ በሽታ ላለባት ሴት ሲሰጡ በምልከታው ሂደት ለማረጋገጥ ችሏል።በማለት በጥናቱ ላይ ጠቁሟል።

በአጠቃላይ መድኃኒቶች ወይም ዕፅዋቶች አብዛኛውን ጊዜ የሚቆረጡት ራሳቸው በተፈጠሩበት ዕለት ነው።ይህም ማክሰኞ ሲኾን እንዴየ ገቢራቸው ደግሞ ዕሮብና ዓርብም ይቆረጣለ።ለምን እነዚህ ቀናት ተመረጡ ሲባል ደግሞ ከላይ እንደ ተባለው ማክሰኞ ዕፅዋት የተፈጠሩበት ዕለት በመኾ ለመዳኅትነት ፈዋሽ በመኾናቸው ሲኾን፤ዕሮብ ደግሞ አይሁድ ጌታቸውን ለመያዝ የመከሩበት ዕለት ሲኾን ዓርብ ደግሞ ጌታቸው የተሰከለውን በማሰብ ነው።

ሐ.የመድኃኒት አሰጣጥ መጠን፡- የኢትዮጵያ የባህል መድኃኒት አሰጣጥ እና መመሪያ እንደመድኃኒት ሰጭው ዕውቀት እና ተግባር ይለያያል፡፡ ዴቪድ (1994፣ 113)

"መድኃኒት ከመስጠት በፊት ስለመድኃኒቱ ምንነት አጠቃቀም እና ሊያስከትለው ስለሚችለው ጉዳት ወይም ጠንቅ የአወሳሰድ መጠን መግንዘብ ያስፈልጋል፡፡ "

ተመስገን (2000) የመድኃኒት አሰጣጥ እና አተገባበር ቢለያይም በዋናነት በመጠጣት፣ በመቀባት፣ በሚሸተት፣ በመማግ፣ በማኘክ፣ በማጨስ እና በክትባት መልክ ተዘጋጅቶ በአንገት ማንጠልጠል፣ በክንድ ላይ ማሰር ናቸው በማለት ገልጸታል፡፡ "በመድኃኒት አጠቃቀም ወይም አሰጣጥ መጠን መለያየት ምክንያት የሚደርሰውን ጉዳት በመግንዘብ ሳታበዛ ወይም ሳታሳንስ ያላዋቂ የጠጣህ እንደኾነ ይጎዳል ይላል (ሐዲስ፣ 1980)፡፡"በመድኃኒት አጠቃቀም ወይም አሰጣጥ መጠን መለያየት ምክንያት የሚደርሰውን ጉዳት በመግንዘብ ሳታበዛ ወይም ሳታሳንስ ያላዋቂ የጠጣህ እንደኾነ ይጎዳል ይላል (ሐዲስ፣ 1980)፡፡ ከዚህ የምንረደው የባህላዊ መድኃኒት አሰጣጥ በዘፈቀደ የማይሰጥ፣ እንደ ዘመናዊ አሰጣት የራሱ የኾነ ህግ ደንብ መኖሩንና በጣም ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት መረዳት ይቻላል፡

2.7.የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ይህ ክፍል ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተያያዥነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶች ለማግኘት የቤተ መዛግብት እና የመረጃ መረብ ዳሰሳ ተደርጓል፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ባይኖራቸውም በተወሰነ ደረጃ የሚያገናኛቸው ጥናታዊ ጽሁፎች ተቃኝተዋል ፡፡ እነዚህ ጥናቶች በቀጥታ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያለቸው ሳይሆኑ በተዘዋዋሪ መንገድ ስለ ርዕሱ ገለፃና ማብራሪያ የሰጡ ዓለም አቀፍ መጣጥፎች (አርቲክሎች) እና በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፣በአድስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና በሌሎች ዩኒበርስቲዎች በሃገረሰባዊ የበባህል መድኃኒት ዙሪያ ተሰሩ ጥናትችን ዳሰሳ ተደርገዋል።

በሙሴ ነቢዩ(2014)" በዕፀ ደብዳቤ ኖኅተ ብርሃን የባህል መድኃኒት አተገባበር ትንተና "በሚል ርእስ አቅርቧል። የምርምሩ ዋና ዓላማ በዕፀ ደብዳቤ ኖኅተ ብርሃን የሚገኙትን የባህል መድኃኒቶችን አተገባበር መርምሯል፡፡ መናፍስት ርኩሳን ማለት ምን ማለት ነው? በዕፀ ደብዳቤ ኖኅተብርሃን የባህል መድኃኒት አተገባበርና የሕመም ዓይነቶች፤ የዕፀዋቱ አገልግሎት ምን ይመስላል? ባህላዊ መድኃኒት ለዘመናዊ መድኃኒት ምን ዐይነት አስተዋጽዖ አበርክቷል፣ አኹንስ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል? የሚሉትን ይዘቶች ከመጽሐፉ አንጻር ፈትሿል፡፡

የጥናቱ አነሣሽ ምክንት ባህላዊ መድኃኒት በዘፈቀደ የሚሰጥ ነው የሚል እና የባህል መድኃኒት መጽሐፍት፤አንዲሁም የባህል መድኃኒት ባለሙያዎች ሕመሙ አንድ ሲኾን የተለያዬ መድኃኒት መኖሩን አይቷል፡፡ የጥናቱ መረጃም በዋናነት በሰነድ ፍተሻ ሰብስቧል፡፡ምርምሩም ከዓይነታዊ የምርመር ዘውግ የሚመደብ ሲኾን መረጃውም በገላጭ ዘዴ ተንትኖ አቅረርቧል፡፡

ለዘመናዊ ሕክምና መሠረቱ ባህላዊ ሕክምና ወይም ባህላዊ መድኃኒት መኾኑ በጥናቱ አረጋግጧል፡፡ አኹን ላይ ዘመናዊ መድኃኒት በመስፋፋቱ በህላዊ መድኃኒት እየተረሳ መምጣቱን ጠቢባን፣ መፍትሔ ሥራይ፣ ጸሎተ ቡዳ እና ጸሎተ ነሐቢ (ሠራተኛ) በቅደም ተከተል አቅርቧዋል፡፡በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ የዕፀዋቶቹ ብዛት እና አገልግሎት እንዲሁም መገኛ ሥፍራዎች እናየሚሰጡት ጥቅሞችም የተገለጹ ሲኾን የሕመም ዓይነቶች፣ መድኃኒቶቹና መገኛ ቦታቸውን፣የሚሰጡት የፊውስ ዓይነትና ገቢራቸውን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ መድኃኒቶቹም በመታጠን፣ በሚቀባ፣በሚዋጥ፣ በመታጠብ፣ በሚጠጣ እና በሚበላ መልኩ እየተመጠኑ የሚሰጡ መኾኑን ጥናቱአረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም ወተት፣ ጠላና ማር፣ ደግሞ ለመድኃኒቱ ማዋሐጃነት እንደሚውሉ እና፤ ነገርግን በሽታው ሲበረታ ማርከሻ ወይም ማስታገሻ እርጎ እና ጠላ መጠጣት አስፈላጊ ነው፡፡እንዲሁም መድኃኒቱ እንዲሠራ ከአልኮል፣ ከሰው ጥላ (ግብረ ሥጋ ግንኙነት ከፈጸመ እና ፀሐይ ሲመተው ቆይቶ ከሚመጣ ሰው) እና ከግብረ ሥጋ ግንኙነት መጠበቅ ግዴታ እንደኾነ ጥናቱ ጠቁማል፡፡

በመጨረሻም ጥንታዊ የባህል መድኃኒት መዛግብትን መልሶ ለማግኘት እናለመመራመር እንደመነሻ ኾኖ እንደሚያገለግል እና ለተጨማሪ ጥናት መነቃቃትን ሊፈጥር እንደሚችል አመላክቷል፡፡በመኾኑም የሙሴ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር በብዙ መልኩ ግንኙነት ሲኖረው የሚለየው ግን እሱ ከአስራ ስድስትእና ከዛ በላይ የበሽታ ዓይነቶችን ሲያጠና የእኔ ግን በሾታላይ በሽታ ብቻ ትኩረቱን ያደረ መኾኑ እና በሾተላይ በሽታም አለመጠናቱ ነው።በተጨማሪም የሙሴ ጥናት በዐፀ ዳብዳቤ ኖኅተ ብርሃን ብቻ ጥቁረቱን ያደረገ እና ስለ ሾተላይ በሽታ አለመጠናቱ ልዩ የሚያድርግ ሲሆን የእኔ ግን በተመረጡ የግእዝ መጽሐፍትን በመጠቀም ስለሾተላይ በሽ ታነው።

ሐብታሙ (2018) በጎንደር ከተማና አካባቢ በሚገኙ የባህል ሃኪሞች ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት ቅመማ፣ አዘገጃጀት፣ በሽታ የመለያ ዘዴና አሰጣጥ ትንተና"በሚል የአቀረበ

ነው።ባህላዊ ህክምና በስሩ በርካታ የባህል መድሃኒት ዘርፎችን ያቅፋል፡፡ በተለይ ከባህላዊ መድሃኒት ዘርፍ ውስጥ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት ከፍተኛውን ድርሻ ወስዳል፡፡ ባህላዊ መድሃኒት ከጥንት ጀምሮ ዛሬም ድረስ በተለያዩ ማህበረሰቦች ዘንድ በህክምናው መስክ ከፍተኛ የሆነ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ሀገረሰባዊ የዕውቀት ዘርፍ መሆኑን አሳይቷል። ጎንደር ከተማም ቀደም ባሉት ዘመናት የስልጣኔ፣ የፖለቲካ፣ የንግድ፣ የሃይማኖታዊ ትምህርት ቤቶች መነሻሪያ እና የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ሆና በመገኘቷ ምክንያት የባህላዊ መድሃኒት ዕውቀቱ ያላቸው ሰዎች በቤተክርስቲያን በኩል ለተለያዩ ትምህርታዊ ተግባራት ወደ ከተማዋ በመግባታቸው የባህላዊ መድሃኒት እንዲስፋፋ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል።

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማም “በጎንደር ከተማና አካባቢ በሚገኙ የባህል ሃኪሞች ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት ቅመማ፤ አዘገጃጀት በሽታ የመለያ ዘዴና አሰጣጥን” አጠቃላይ ሁኔታን መርምሯል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በዒላማዊ የንሞና ዘዴ የተመረጡ በጎንደር ከተማና አካባቢ የሚኖሩ ስምንት ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት አዋቂዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የባህል መድሃኒት አዋቂዎች በዒላማዊ የንሞና ዘዴ የተመረጡትም ስለ ባህላዊ መድሃኒት ከፍ ያለ ዕውቀትና የተሻለ መረጃ ያላቸው በመሆናቸው ገልጿል፡፡ ከእነዚህ የጥናቱ ተሳታፊዎች መረጃ የተሰበሰበው ደግሞ በተሳትፏዊና ጽሞናዊ ምልከታዎች እና በቃለ መጠይቅ ተጠቅሟል።

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማም “በጎንደር ከተማና አካባቢ በሚገኙ የባህል ሃኪሞች ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት ቅመማ፤ አዘገጃጀት በሽታ የመለያ ዘዴና አሰጣጥን” አጠቃላይ ሁኔታን መርምሯል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በዒላማዊ የንሞና ዘዴ የተመረጡ በጎንደር ከተማና አካባቢ የሚኖሩ ስምንት ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት አዋቂዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የባህል መድሃኒት አዋቂዎች በዒላማዊ የንሞና ዘዴ የተመረጡትም ስለ ባህላዊ መድሃኒት ከፍ ያለ ዕውቀትና የተሻለ መረጃ ያላቸው በመሆናቸው ገልጿል፡፡ ከእነዚህ የጥናቱ ተሳታፊዎች መረጃ የተሰበሰበው ደግሞ በተሳትፏዊና ጽሞናዊ ምልከታዎች እና በቃለ መጠይቅ ተጠቅሟል።

በተግባራዊ የትውር ንድፈ ሃሳብ ላይ በመመርኮዝ በዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ተጠቅሟል።፡ የተገኙት መረጃዎችም በይዘትና ገላጭ የመረጃ የመተንተኛ ዘዴዎች ተተንትነዋል፡፡ በጥናቱ ሂደት ባህላዊ ሃኪሞች ከተለያዩ የዕፅዋት ዓይነቶች ባህላዊ

መድሃኒት ለማዘጋጀትና ተገቢውን የባህል መድሃኒት ለህሙማን ለመስጠት የበሽታውን ዓይነት ባህላዊ በሆነ መንገድ እንደሚለዩ ለማረጋገጥ ችሏል። የበሽታውን ዓይነት ከለዩ በኋላም የመድሃኒት ዕፅዋቱን ለመሰብሰብ አንድም ከዕፅዋቱ ተፈጥሯዊ አካባቢ፣ አንድም ከመኖሪያ አካባቢያቸው ካላመዷቸው ዕጽዋቶች፣ አንድም ዕፅዋቱን በመግዛትና ከሌላ ባህላዊ ሃኪም ጋር በመለዋወጥ የሚያገኟቸውን የመድሃኒት ዕፅዋቶች ይጠቀማሉ።። ዕፅዋቱን በመሰብሰብ ሂደትም ለባህላዊ ዕፅዋት መቁረጫ፣ ስር መቆፈሪያና ማዘጋጃ (መቀመሚያ) የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ ቁሳዊ ባህሎችና ዕፅዋቱ ለተገቢው ዓላማ እንዲሰምር ሲባል የሚደረግ የዕፅ ማንገሻ ጸሎት የአላቸው መሆኑን ገልጿል።።

በተጨማሪም የባህላዊ መድሃኒት ዕፅዋቱን ከመገኛ ቦታቸው ለመሰብሰብና የመድሃኒቶቹን ፈዋሽነት ለማጠናከር የሚያገለግሉ የተለያዩ ልማዳዊ ድርጊቶች ወይም ሃገረሰባዊ ክዋኔዎች አከናውኗል።። በዚህ ጥናት የተካተቱ የመረጃ አቀባዮች ዕምቅ የሆነ የባህላዊ ዕፅዋት መድሃኒት ዕውቀት ባለቤቶች ሲሆኑ፣ ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒቱን ዘመናዊ በሆነ መንገድ የሚሰራበት ሁኔታ በሚመለከተው አካል ቢታሰብበት አሁን በህክምናው መስክ ያለውን ዕድገት ወደ በለጠ ደረጃ ሊያሻሽለው የሚችል መሆኑን እና የዕፅዋት መድሃኒቱንም ከመጥፋት መታደግ እንደሚገባ ጥናቱ ጠቁማል።።ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ከእኔው ጥናታዊ ጽሑፍ የሚለየው በጎንደርና አካባቢው ብቻ ጥናትና ምርምሩን አደርገዋል የእኔ ጥናትና ምርምር ግን በተለያዩ መጽሐፍ ውስጥ ያለውን የሾተላይ መድኃኒት ይተናትናል።ይህ ጥናት በተጨማሪም በሀገር በቀል መድኃኒተኞች/ጥበበኞች/ን መሠረት ሲያደርግ የእኔ ጥናት ግን በሾተላይ በሽታላይ እና የመድኃኒቱ ትግበራ ላይ ይተነትናል።

ምሕረት(2000)፣በአዲስ አበባ ከተማ የሚሰጠውን ባህለዊ መድኃኒት ሕክምና በሚማለከት አቅርቧል።የባህለዊ ሐኪሞች የሕክምና መነሻ፣የመድኃኒቶች መገኛና አዘገጃጀት እንዲሁም ታካሚን አካቶ አቅርቧል።የዚህ ሥራው ዓለማውምየዘመናዊ ሕክምና በስፋት የሚሰጥበትን ምክንያት በመረጃ ለይ ተመስርቶ የሕክምና አሰጣጥን በመከታተል ውጤታማነትን ከታካሚዎች ማረጋገጥ ችሏል። በተጨማሪም እምነት በባህለዊ ሕክምና ያለውን ሚና አሳይቷል።

ጥናቱን ያካሄደውም የባህል ሐኪሞችን፣ታካሚዎችን የዘመናዊ ጤና ባለሙያውችን በቃለ መጠየቅበባህለዊ ሕክምና መስጫ ቦታዎች ተገኝቶ ምልከታ አደርጓል።ነገር ግን ሰነድ ፍተሻን በውስጡ ቢጠቀምም ከጥናቱ ዘዴዎች ለይ ግን አልጠገለጸም።እስከ ሦስት መቶ

የሚደርሱ የባሕለዊ መድኃኒት ባለሙያዎች መኖራቸውን በእያንዳንዱ ሐኪም ደግሞ ቢያንስ በቀን አስር ታካሚ እንደሚገኝ መረጃዎችን ሰብስቧል። አካለዊ ቁስል ጋር የተያያዙ በሽታዎችን እንፈወሳለን ስለሚሉ አብዛኛዎቹ ታካሚዎች የሰውነት ቁስል ያለባቸውን ከመድኃኒት መሰባሰብ ጀምሮ እምነት የሐኪሞችም ኾነ የታካሚዎች የፈውስ መነሻን ለይቶል።

የባህለዊ መድኃኒት ባለሙያዎች ሁሉምበቂ ችሏታ ያላቸው ታማኝ ባይባልም፣ ዘርፉ የሚሰጠውን አገልግሎት ከፍተኛ ስለኾነ በዘመናዊ የሕክምና ባለሙያዎች ታግዞ ቢቀጥል ያለውን የጤና ችግር ለማቀለል አሰተዋጽዖ የጓላ ነው በማለት የይሁንታ ሀሳቡን ሰጥቶል።ይህ ጥናት አብዛኛውን ጥናቱን በቃለ መጠይቅ መረጃ አሰባሰብ የተጠቀመ ሲኾን ሰነድ ፍተሻን እንደ ተጠቀ ጥናቱ ይጠቁማል ይሁን እንጂ ከጥናቱ አጠናን ዘዴ ለይ በንዑስ አንቀጽ ተከፋፍሎ አለስቀመጠም።ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ከእኔው የሚለየው የሚጠኑት መድኃኒትች ከምን መጽሐፍ እንደኀነ አልተገለጸም።በተጨማሪም አጥኚው ጥቁረቱን ያደረገው በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ መሆኑ ነው።

ተመስገን በየነ (2012) የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር ትንተና በደቡብ ጐንደር ዞን ማኅበረሰብ" በሚል ርእስ ጥናት አቅርቧል፡፡ የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ በአማራ ክልል በደቡብ ጐንደር ዞን ውስጥ በሚገኙ ሦስት (ፋርጣ፣ ሊቦ ከምከም እና እብናት) ወረዳዎች ላይ ትኩረት በማድረግ የደቡብ ጐንደር ማህበረሰብን የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር ሂደትና ተግባር ምን እንደሚመስል መመርመርና የባህል ልማዱን ማስረዳት ነበር፡፡ በጥናቱ ሂደትም በባህል ሕክምና/በማኅበረሰቡ እሳቤ የሕመም መንስኤ ምንድን ነው? በባህል ሕክምና ዕውቀት የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች ምን ምን ናቸው? የጤና ኃይል ሚዛን ማስተካከያ ስልቶች እንዴት ይከወናሉ? በባህል ሕክምና ልማድ የዕፀ መድኃኒት አሰባሰብ ቅመማና አሰጣጥ ሥርዓት ዐውዳዊ ክዋኔ እንዴት ይተገበራል? የባህል ሕክምና ዕውቀት ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ምን አስተዋፅዖ አለው? የማኅበረሰብ ልማድ ሥነ-ምህዳርንእንዴት አስጠበቀ/አራቆተ? ለምን? ለሚሉ ጥያቄዎች በጥናቱ ይዘት መልስ ሰጥቷል፡፡ እነዚህንየምርምር ጥያቄዎች ከግብ ለማድረስ ገላጭ ትንተና ስልት እና ዓላማ ተኮር ናሙናን መሠረት ያደረጉ ሲኾን የመስክ መረጃዎችን በምልከታና በቃለመይቅ ሰብስቧል፡፡

በጽንሰ ሐሳብ ደረጃም ፎክሎር (ባህል) ጤና እና ሕመም፣ የባህል መድኃኒት፣ የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር፣ የባህል ሐኪም ማንነት፣ የባህል ሕክምናማሕቀፍ እና ምድብ፣ በባህል ሕክምና የበሽታ መንሥኤ እሳቤ፣ በባህል ሕክምና የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች፣ የባህል መድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ ክዋኔ እና ሥነ ምህዳር የሚሉትን በጥናቱ አብራርቷል፡፡

በደቡብ ጐንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች በአካባቢያቸው የሚገኙ የሥነ-ምህዳር ዓይነቶችን በመለየት ከዕፀዋት፣ ከእስሳት፣ ከማዕድናትና ከአዕዋፍ የሰበሰቧቸውን ግባቶች ሲቀምሙ በማድረቅ፣ በመውቀጥ፣ በመሰለቅ፣ በመዘፍዘፍ፣ በመለየት፣ከዕፀዋት፣ ከእንስሳት፣ ከማዕድናትና ከአዕዋፍ፣ የሰበሰቧቸውን ግባቶች ሲቀምሙ በማድረቅ፣በመውቀጥ፣ በመሰለቅ፣ በመዘፍዘፍ፣ በመቀቀልና በማጥለል፣ አዘጋጅተው በሚጠጣ፣ በሚሸተት፣ በሚታሸክ፣ በሚጨስ፣ በሚቀባ መልኩ እንደሚሰጡ ከባለሙያዎች በቃለ መጠይቅ አረጋግጧል፡፡የደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ እምነቶች (ደንቃራ፣ መተት፣ አንደርቢ፣ ተፈጥሮን መርዳትና የመቆጣጠር ኃይል፣ የበሽታ ሽኝት፣ የዓለሞቹ/ወተቱ በሽታ ሥርዓትና አተገባበር ልማድ) እዳላቸው አጥኚው ጠቁሟል፡፡ በዞኑም ጐልተው ከሚከሰቱ በሽታዎች መካከል፣ የጉበት/ የወፍ በሽታዎች፣ ስንፈተ ወሲብ፣ ኪንታሮት፣ የወባ በሽታ፣ ቁርጥማት፣ የቆላ ቁስል፣ ጥገኛ ትላትል/ወስፋትና የኮሶ ትል፣ እከክ፣ የስኳርና የኩላሊት ሕመም፣...በዋናነት እንደሚከሰቱ ገልጿል፡፡ሌለው ደግሞ የደቡብ ጐንደር ዞን ማኅበረሰብ እሳቤና መረጃ፣ ለሕመም መንሥኤ አጋንንት ወይም ርኩሳን መናፍስት ሲኾኑ ዲያቢሎስ፣ ጋኔል፣ ጅን፣ ዛር፣ ቡዳ፣ ብሂሞት፣ በመባል ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ መናፍስት በዐየር፣ በዛፍ፣ በወንዝ፣ በተራራ፣ በባሕርና በመሬት ተበትነው እና ተሰራጭተው ስለሚገኙ፣ የዐየር፣ የመሬት እና የባሕር ርኩሳን መናፍስት ተብለው እንደሚጠሩገልጿል፡፡በባህል ሕክምና ዕውቀት የሚተገበረው የበሽታ መለያና መመርመሪያ ዘዴዎች ምን ያህል ውጤታማ እንደመኾኑ በዘመናዊ ሕክምና ሳይንስ በንጽጽር ቢጠኑ፣ በመድኃኒት አሰጣጥ ሂደትም የበሽታ ዓይነትና ባሕርይ ብላ/አትብላ የምግብ ምርጫና ክልከላ ከምግብ ንጥረ ነገር ይዘትከበሽታው ዓይነት ጋር ምን ዓይነት ተዛምዶ እና ተቃርኖ እንዳላቸዉ በንጽጽር ቢጠኑ፣ የዘርፉን ክፍተት ለመሙላት አበርክቶ እዳላቸዉ ይታሰባል ሲል የይኹንታ ሐሳቡን በማቅረብ ጥናቱን አጠናቋል፡፡የተመስገን ጥናት በደቡብ ጎንደር ዞን የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ-ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር ሂደት፣ ተግባር፣ ገለጻና የመረጃ

ዓይነት፣ ክለሳ ድርሳን እና ትንተና ክፍል ጠንካራና በሥርዓት የተደራጁ ናቸው፡፡ መናፍስትን በተመለከተ ተፈጥሯቸውን እና ግብራቸውን ለመረዳት ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸዉ ግለሰቦች በዘልማድ እንጅ መሠረታዊ ዕውቀት ያላቸው አይመስልም፡፡ስለዚህ አጥኚው በጥልቀት ለመረዳት የሥነ-መለኮት ተመራማሪዎችን እና የመጻሕፍት መምህራን ስለመናፍስት አለመጠየቁ የጥናቱን ክፍተት ያመለክታል፡፡ የእኔ ጥናት ከተመሰገን የሚለየው የደቡብ ጎንደር ዞንን የባህል ሕክምና ዕውቀት እና የሥነ ምህዳር ዐውዳዊ መስተጋብር ማጥናቱ ልዩ ቢያደርገውም በቃለ መጠየቅ እንጂ መጽሐፍትን አልተጠቀመም በመኾኑም ይህ ጥናት ግን የተለያዩ መጽሐፍትን በማየት የሾተላይ በሽታን ማጥናት ነው።

ምዕራፍ፡ሦስት የአጠናን ዘዴ

3.1.የጥናቱ ዘዴ

ማንኛውም ጥናትና ምርምር በሚካሄድበት ጊዜ እንደየ ርእሱ የጥናት ዘዴን የተከተለ ነው። በዚህ ክፍል ጥናቱ በምን ዓይነት ዘዴ እንደ ተከናወነ የሚዳስስ ሲኾን በውስጡም የጥናቱ ዓይነት፣ የመረጃ ምንጮች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እና የመረጃ መተንተኛ ዘዴ የሚሉ ንዑሳን ክፍሎች አሉት፡፡ እነዚህም ራሳቸውን ችለው እንደ ሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል።

3.2.የጥናቱ ዓይነት

ይህ ጥናት የሚከናወነው የተሰበሰቡ የሰነድ መረጃዎች እና ተዛማጅ ጽሑፎችን በመጠቀም የተመረጠውን ርእስ በዝርዝር እና በጥልቀት በመመርመር በመኾኑ ከዓይነታዊ የምርምር ዘውግ የሚመደብነው።

ዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ከቁጥር ይልቅ ያንድን ነገር ከትርጉም ፣ከፅንሰሐሳብ፣ ከውክልና እና ካጠቃላይ የቁሱ ምንነት ላይ የሚያተኩር በመኾኑ ጥናቱ በዓይነት ላይ እንጂ በመጠን ላይ መሠረት አያደርግም፡፡ ምክንያቱም" ዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ሲኾን አጥኚው ናሙናዎችን ለመምረጥ ጥናቱ ከሚያተኩርበት በተወሰኑ ጉዳዮች ብቻ ላይ ያለውን አስተሳሰብ ማንጸባረቅ እንዳለበት በርግ(2001፣2-3)ይገልጻል፡፡" ያለው ሙሴ ነቢዩ በዋቢነት ተጠቅሞ በጥንተናቸው ላይ ገልጸዋል ። ስለዚህ የጥናቱ ሥነዘዴ ዓይነታዊ በመሆኑ ለመተርጓም፣ ለመተንተን፣ ለመግለጽ፣ለማብራራት፣ከስሌታዊ ይልቅ ዓይነታዊ የጥናት ዘዴን ተጠቅሜለሁ።

3.3.የናሙና አመራረጥ ዘዴ

ይህ ጥናት ለእኔ ጥሩ ግብዓት እና ውጤት የሚሰጡ ተሳታፊዎችን በአላማ ተኳር (purposivesampling) የናሙና አመሩረጥ ዘዴን ተጠቅሜዋዋል።ስለ ባህላዊ ሕክምና መድኃኒት ያውቃሉ ተብለው ተለይተው የተመረጡ አራት የባህላዊ ሐኪሞች እና አንድ የዘመናዊ ሐኪም ተመርጠዋል።እነዚህም የባህላዊ ሐኪሞችም ከሰባት እስከ አሥራ አምስት በላይ ልምድ ያላቸው፤ በአንድምታ(አስተያየት፣ ትርጓሜ)፣በቅኔ እና በአዲስ ኪዳን አተረጓጎም ባለሙያዎች በመሆናቸው ነው። በመንፈሳዊ መድኃኒቶችም ጭምር ልምድ ያላቸው ተመራማሪዎች ናቸው። ይህ የተመረጠ ዘዴ በጥናቱ ግቦች ጋር ተያይዞ ትርጉም

የሚያብራራ እና በአካባቢው የሚስተዋለውን ለሾተላይ የተሞላ መረጃ ለመስጠት የሚችሉ ባለሞያዎችን እና ተሳታፊዎችን እንዲካተቱ አረጋግጧል።

3.4.የመረጃ አመራረጥ ዘዴ

በዚህ ጥናት ከተመረጡት የግእዝ የመድኃኒት መጽሐፍት ርእሰ ጉዳዩን የሚያወሱበት ለይም ከጥናቱ ጋር ግንኙነት ያለቸውን የመረጃ መጽሐፎች ተመርጠዋል።እነዚህ ባህላዊ የመድኃኒት መጽሐፎችም በሾተላይ መድኃኒት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ተብለው ስለሚታመኑ ተመርጠዋል።በተጨማሪም የባህላ ዊመዴኃኒት ሐኪሞች፣ተመራማሪዎች እና ታካሚዎች በኣላማ ተኮር (purposivesamplin) አማካኝነት ተመርጠዋል።ከእነዚህ ተሳታፊዎች መረጃ በ (semi-structuredinterviews)ተሰብስቦ በጉዳዩ ላይ ትልቀት በጉዳዩ ማብራሪ ተስትዶል።

3.5.የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች

የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ የጥናቱን ጥያቄዎችን ለመመለስ እና የጥናቱን ዓላማ ለመፈፀም ሲባል ለጥናቱ አትጋቢ ምላሽና ለጥናቱ ማሳካት አስተዋፅኦ አለቸው ተብለው የሚታመኑ መሣሪያዎች የሚሰባስቡት ክፍል ነው።ይህንን አስመልክተውም ሐይማኖት (2025)በጥናታቸው ላይ የሚከተለውን ብለዋል።

“According to Yaleu (2011), common data collection methods include written questionnaires, oral questionnaires, observation, document inspection, tests, and group discussions. For this

study, document analysis and semistructured interviews were employed as the primary data collection tools. The researcher has utilized both primary and secondary sources for data collection:"

እንደ Yaleu (2011)ገለፃ፣መረጃን ለስብስብ የሚያገለግሉ የጹሑፍጥያቄዎች፣፣ የቃል መጠይቆች፣ ምልከታ፣ ሰነዶችን መመርመር፣ ፈተናዎች እና የቡድን ውይይቶች ናቸው። ለዚህ ጥናት ዋና የመረጃ ስብስብ መሣሪያዎች እንደመሆናቸው የሰነድ ትንተና እና ከፊል-የተዋቀሩ ቃለ-መጠይቆች ተጠቅመዋል። ተመራማሪው መረጃ ለመሰብሰብ ዋና (Primary) እና ሁለተኛ (Secondary) ምንጮችን በእንድነት ተጠቅመዋል።

ስለዚህ ይህ የጥናቱ ርእሰ ጉዳይ ሹለት የተለያዩ ንኡሳን ጉዳዮችን የያዘ ነው።እነዚህም የሚከተሉት ናቸው።

3.5.1 Primary sources: የቀደማይየመረጃምንጭ

በቀዳማይ ምንጭነት እኔ የምጠቀመው በተመረጡ የግእዝ መጽሐፍትን እና ከፊል የተደረጀቃለ መጠይቅ ነው።። መጽሐፈ መድኃኒት፣መጽሐፈ መድሐኒት ፣ዕፀ ዳብዳቤ፣መጽሐፈ አድኅኖት እና መጽሐፈ ፈውስ በግእዝና በአማርኛ ከተጻፉት መጽሐፍት መካከል በዋና ምንጭነት የተጠቀምኩቸው ሲኾኑ የወረጥኳቸው ምክንያትም መጽሐፎቹ በውስጡ የያዛቸው የዕፀዋት መድኃኒቶች በሌሎች ተዛማጅ ጥናቶች አብዛኛዎቹ ያልተጠኑ በመኾናቸዉ እና እኔም በተግባር የማውቃቸዉ የመድኃኒት ዓይነቶች በውስጡ ስለተካተቱ ነው።። በተጨማሪም ከእነዚህ መጽሐፍት ላይ የምነናገኘው እና እራሱ ሾታላይ በሽታው በሌሎች አጥኒ አካላት ስላልጠና ነው።በመኾኑም የተጠቀምኩት በአውሮፓ ውስጥ ካሉት Griaule(ግሩል) ከሰበሰባቸዉ የብራና መጻሕፍት ውስጥ በብሩቲሽና በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትንየአማርኛና የብራና መጽሐፍ ከመረጃ/በበይነ-መረብ/BnF-በማውረድነው።

ተ.ቁ.	መለያ	የሰነድ አይነት
1	(IES,2444)	መጽሐፈ መድኃኒት
2	(BMO,828)	መጽሐፈ መድኃኒት
3		ዕፀ ዳብዳቤ
4	መአ፣2010	መጽሐፈ አድኅኖት
5	(ETHIOPIEN402GURIAULE98)	መጽሐፈ ፈውስ

ለቀዳማይ ምንጭነት የተመረጡ የመጽሐፍት አይነትች

3.5.1.1.የሰነድ ትንታኔ

የሰነድ ትንታኔ በግእዝ የተጻፉ ባህለዊ የመድኃኒት መጽሐፍትን በመመርመር ለሾተላይ በሽታ በቂ የሆነ ባህላዊ ምርመራን የሚሰጡ መረጃዎች ተወስደዋል።ይህ ዘዴ ታሪካዊ እና ባህላዊ ማዕቀፍ በተስተካከለ ሁኔታ ሲታይ በባህላዊ መድኃኒቶች እና በየተግባራቸው ላይ የተሻለ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዲኖኝ አድርጓል።የተመረጡ መጽሐፍትም እንደ መጽሐፈ

መድኃኒት (IES2444)፣መጽሐፈመድኃኒት(BMO,828)፣ዕፀ-ዳብደቤ፣መጽሐፈ አድኅኖት(መአ፣2010)፣መጽሐፈ ፈወስ(ETHIOPIEN 402 GURIAULE 98)ናቸው።

ከላይ ከተጠቀሱት የመረጃ ምንጮች በተጨማሪ መረጃ የሚሰበሰቡበት መንገድ ደግሞ በዋናነት ሥራ ላይ የሚውለው ሰነድ ፍተሻ በመኾኑ ቤተ-መጻሕፍት የሚገኙና ከግል በግኽር፣ከግለሰቦች ደግሞ በትውስት መልክ የተገኙትን መጻሕፍት እና ጥናታዊ ጽሑፎችን በመጠቀም ከተመረጠው ርእሰ ጉዳይ ጋር ተዛማጅ ጉዳዮችን በመፈተሽ ጥናቱ ተቀናውኖል።

3.5.1.2.ቃለመጠየቅ

ስለ ጉዳዩ በቂ እውቀት ወይም ግንዛቤ አላቸው ተብሎ የሚታሰ ሰዎችን ለጥናቱ ማሳካት ጉልህ ሚና ያላቸው መረጃ ሰጪዎችን በከፊል (semi-structuredinterviews) በመጠየቅ መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ ነው፡፡ እንዲሁም ቃለ መጠይቅ ጠያቂው እና ተጠያቂው በአካል ወይም ፊት ለፊት በመገናኘት መረጃ የሚለዋወጡበ ትሂደትነው፡፡

"Face to face interview enables the researcher to establish rapport with potential participants and there fore gain their cooperation.It allows the researcher to clarify Ambiguous answers and when appropriate,seek follow up information (LeedyandOrmrod2001፡29)።"ፊት ለፊት የሚደረግ ቃለመጠይቅ ተመራማሪው ሊሳተፉ ከሚችሉ ተሳታፊዎች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር እና ስለዚህ ትብብር እንዲያገኙ ያስችላቸዋል።ተመራማሪው አሻሚ መልሶችን እንዲያብራራ ያስችለዋል እና አስፈላጊነው ይላሉ፡፡

ልቅ ወይም ያልተደራጀ ቃለመጠይቅ ምላሽ ሰጪዎች ልምዳቸውን እንዲናገሩ የሚመስላቸውን ክስተቶች እንዲገልፁ፣ ለሁኔታዎች ራሳቸው ፍቺ እንዲያቀርቡ እና የራሳቸውን አማራጮች ና አመለካከቶች እንዲገልፁ የሚያበረታታ በጣም አስፈላጊ የቃለመጠይቅ ዓይነትነው፡፡ በመሆኑም በዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ስለበሽታ አስከፊነት፣ ስለበሽታው ምንነት፣ ስለመድኃኒት ምንነት፣ ስለመድኃኒት አዳኝነት ምን እንደ ሚመስል መረጃው ተሰብስቧል።

3.5.1.3.መረጃ ሰጪዎችን አመራረጥ ዘዴ

መረጃ ሰጪዎች ከባህላዊ መድኃኒት ህክምና ጋር በተያያዘ መልኩ የታሪካዊ እና የባህላዊ ችሎታቸውን መሠረት በመድረግ ተመርጠዋል። አንዳንዶቹ ረጅም ዓመታት ልምድ ያላቸው የባህላዊ መድኃኒት ባለሙያዎች ናቸው፣ አንዱ የልዩ ሐኪም ይሆናል፣ ሌሎች ደግሞ በአንድምታ አስተያየት ባለሙያዎች፣ቅኔ ባለሙያ እና የአዲስ ኪዳን ትርጓሜ ተመራማሪዎች ናቸው።

ከዚህም በመነሣት በአማራ ክልል በአዊ ዞን ሦስት እና በአቸፈር ከተማ ወረዳ አንድ የባህል ሐኪሞች መካከል አራት ግለሰቦችን ለጥናቱ በመለየት፣ ከዳንግላ ወረዳ መሪጌታ ነቢዩ፣መሪጌታ ዳኔኤል እና መሪጌታ ጸገየ አበበ፣ ከአቸፈር ወረዳ መሪጌታ ፀጋየ ፈንቴ ተመርጠዋል። የተመረጡበት ምክንያትም ከላይ እንደ ተገለጸው ከሌሎች የባህል መድኃኒት ባለሙያዎች ማለትም በአንድምታ ትርጎሜ፣ በቅኔ ባለሙያ እና የአዲስ ኪዳን ትርጓሜ ተመራማሪዎች እና በእውቀታቸው የተሻለ በመኾናቸው በሾተላይ መድኃኒት ዕፀዋቶችን በጥልቀት እና በዝርዝር ያሰረዳሉ ተብሎ ስለታመነባቸው ነው።

በተጨማሪም በዚሁ ከተማ ዳንግላ ሆስፒትል በነርሲንግ ሙያ ያላቸው አስራት ታምር በቃለ መጠይቁ ተካተዋል። ቃለ መጠይቁ ሲደረግ አጥኚው የተጠቀመው መሳሪያ ማስታወሻ ደብተር ብቻ ነው፡ምክንያቱም ቃለ መጠይቅ የሚደረጉት ባለሙያዎች በሌሎች መሳሪያዎች ፈቃደኛ ባለመኾናቸዉ ነው።በተለይም ምሥጢራዊ እና ድብቅ የሚባሉ ዕውቀቶችን ለጥናቱ አስፈላጊ እና ዝርዝር መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነፃ ቃለ መጠይቅ በዋናነት ተግባራዊ ተደርጓል።

3.5.2.የካልኣይ የመረጃ ምንጮች

በካልኣይ ምንጭነት ሥራ ላይ የሚውሉት ደግሞ ከዚህ በፊት የተጠኑ ጥናቶች እና የተጻፉ ሰነዶች ሲኾኑ ለዚህ ጥናት ዓላማ ሲባል በሾተላይ በሽታ ዙሪያ የተጻፉ የግእዝ የባህል መድኃኒት መጽሐፍትንም ቁምር እና የተለያዩ በግእዝ ቋንቋ የተጻፉ የባህል መድኃኒት መጻሕፍትን ወደ አማርኛ በመቀየር፤ እንዲሁም በእንግሊዝኛ እና በአማርኛ በሀገር ውስጥ እና በሀገር ውጭ ሰዎች የተጻፉ መጻሕፍትን እና የተደረጉ ጥናቶችን፣ በተጨማሪም፤ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን፣የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትን፣የአማርኛ መዝገበ ቃላትን፣እና ሌሎች የቀደምት የባህል መድኃኒቶች መጻሕፍትን በመረጃ ምንጭነት ተጠቅሜለሁ።

3.6. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

ይህ ጥናት ዓይነታዊ እንደመኾኑ መጠን በሰነድ ፍተሻ እና በቃለ መጠይቅ በንጥል ጥናት የተሰበሰቡ መረጃዎችን በዓይነት እና በይዘት በመመደብ ትንተና ተካሂዳል።በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለመተንተን የተመረጠው ዘዴ ገላጭ እና የይዘት ትንተና (Content Analysis) ሲኾን በመረጃዎቹ መካከል የሐሳብ ዝምድና እና መመሳሰልን በመመርመር፣የዕውቀቱን መሠረት እና ማሕቀፍ ማደራጀት ይቻላል። በአደረጃጀቱም ሂደት የጋራ የኾነ ምድብ (pattern) በማደራጀት በተግባር እና በዝምድና የሚገናኙትን ዐውድ በመለየት ማዋገን ነው። በተጨማሪም የበሽታውን መንስኤ እና የመድኃኒቶችን አዳኝነት እና ተግባር በመመርመር እና እነዚህ ኹነቶች የሚከሰቱበትን እና የሚተነተኑበትን ተግባር መነሻ በማድረግ ለትንተና ማቅረብ ነው። በሽታዎች፣ መድኃኒቶች እና ተግባሮቻቸዉ የሚከናወኑት የተሰበሰቡ የሰነድ መረጃዎች እና ተዛማጅ ጽሑፎችን በመጠቀም የተመረጠውን ርእስ በዝርዝር እና በጥልቀት በመመርመር በመኾኑ ከዓይነታዊ የምርምር ዘውግ የሚመደብ ነው።

3.7. የግእዝ እና አማርኛ የመድኃኒት መጽሐፍት

የዚህ የሾተላይ በሽታ መድኃኒት መመረቂያ ጽሑፍ የተመረቱ ዋና ዋና የሚከተሉት መጽሐፍትን በመጠቀም ትንተናው የተሰጠበት ነው።መጽሐፈ መድኃኒት(IES 2444)፣መጽሐፈ መድኃኒት (BmO.828)፣ዕፀ-ዳብዳቤ፣መጽሐፈ አድኅኖት(መአ፣2010)እና መጽሐፈ ፈውስ (ETHIOPIEN 402 GURIAULE 98) ናቸው።

3.8. የግእዝ እና አማርኛ የመድኃኒት የመጽሐፍቱ ውጫዊ እና ውስጣዊ ዝርዝር መግለጫዎች (Physical and Content Description of the Manuscript)

3.8.1 መጽሐፈ መድኃኒት(IES 2444)



ፎቶ ግራፍ 1 የመጽሐፉ መድኃኒት ስዕል/lES 2444፣f.109v እና f.119r-120v

የመጽሐፉ ዝርዝር መግለጫ		
ቁጥር	ዝርዝር	መግለጫ
1	መለያ	ርእስ መጽሐፈ መድኃኒት(የፈውስ መድኃኒት መጽሐፍ) ደራሲ ወይም ጻሓፊ፡ኤርምያስ ነብዩ የመጽሐፉ አይነት፡ባህላዊ የመድኃኒት መጽሐፍ

2	ውጫዊገጽታ)	ማቴሬያሉ፡ብራና የመጽሐፉ ሽፋን፡ከእንጨት የተሰራ የቀለም አይነት ፡ቀይቀለም የመጽሐፉ መጠን፡ያልጠወቀ የመጽሐፉ ቅርፅ፣ ከሬ ሁኖ አራት ማዕዘን የረቀት ብዛት (folio)፡163) የውጭ ተባቂ ወረቀቶችን

		ጨምሮ አቀራረብ(Layout)፡ከ1-2 ኮለኖች መስመር በእያንዳንዱ ገጽ ከ25-27 የተወሰነ ነው
3	Paleographical Feature የጽሕፈት ሁኔታ	የተጻፈው፡ግእዝ እና አማርኛ የእጅ ጽሑፍ፡ተመሳሳይ ሁኖ በደማቅ የተጻፈ ይዘቱ የተጻፈው ቀለም፣ጥቁር እና ቀይ የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣በመጨረሻ አራት ነጥብ ሐረግ ወይም ስዕል፣የለውም footnot(የግርጌ መግለጫ)፣የለውም
4	የጽሑፉ ይዘት	incipit(መግቢያ)በስመ አብ ወወልድ ፩ አምላክ፣መጽሐፈ መድኃኒት ዘጸሐፈ ኤርሚያስ ነቢይ ለራስ ምታት---- "በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ፣ነቢዩ ኤርሚያስ የጸሐፈው መጽሓፈ መድኃኒት እንዲህ ይላል----" Explicit/መደምደሚ/፣...ደም ለፈ[መ]ታት ሴት ጥቁር ጠለጅ፤ የዝረፋው እንቡይ፤ ያሸክት፤ የውሾኝ፤ የቱልት የሸረሪት ድር ጨምረህ ከክንዲ ትሰር የተጻፈው ቋንቋ፣ግእዝና አማርኛ ባዶ ቦታ የለውም

ሠንጠረዥ 2 የመጽሐፈ መድኃኒት (IES.2444) ውጫዊና ውስጣዊ መግለጫ

ማጠቃለያ፣ይህ የብራና የመድኃኒት መጽሐፍ ባህላዊ የህክምና ጽሑፍን የያዘ ሲሆን ጸሓፊውም ኤርሚያስ ነቢዩ ነው።የተጻፈው በግእዝ እና በአማርኛ ቋንቋ ነው.።የመጽሐፉ ሽፋን ከእንጨት የተሠራ እና ቀይ ቀለም ያለው ሲሆን መጠኑ ያልታወ፣ቅርፅ-አራት ማእዘን ያለው፣የገጽ (folio) ብዛት : 163 (የጥበቃ ቅጠሎችን ጨምሮ) የያዘ ነው። ባለቤት ያልታወቀ።የተጻፈው ዘመን(century)፡20 ሲሆን አምዱ ደግሞ አንድ እስከ ሁለት ነው።የእጅ ጽሑፍ ተመሳሳይ እና በደማቅ መልኩ የተጻፈ ፣ጸሓፊውም ቀይና ጥቁር ቀለማትን በመጠቅም ጽፏል።አጠቃላይ ሁኔታ በጽሑፉ መጨረሻ ላይ ደግሞ አራት ሙሉ ማቆሚያዎች እና ነጥቦች አሉት። ይህ የእጅ ጽሑፍ ብራና ከመሆኑም በላይ 25-27 መስመሮችን የያዘ ነው።እያንዳንዱ መስመር በአማካይ ሶስት ቃላትን ይዞል ።እያንዳንዱ ቃል 2,3,4,5 ወይም 6 ፊደላት አለው ቢኖራውም ቋሚ ግን አደለም።በመጀመሪያም ሆነ በመጨረሻ ሐረግ፣footnot፣ የለውም።አጀማመሩ በሰመ አብ ወወልድ አሀዱ አምላክ መጽሐፈ መድኃኒት----ብሎ ሲጀምር መዝጊያ Explicit/መደምደሚው/ደግሞ...ደምለፈ[መ]ታት ሴት ጥቁር ጠለጅ፣የዝረጭ እንቡይ፣ያሸክት፣የውኾኝ፣የቱልት የሸረሪት ድር ጨምረህ ከክንዲ ትሰር በማለት ይዘጋል።

3.8 2 መጽሐፈ መድሐኒት (BMO, 828)



ፎቶግራፍ 2 መጽሐፈ መድሐኒት/የመድኃኒት መጽሐፍ ብሪቲሽ 828/አንቀጽ 59/

ይህ የመድኃኒት መጽሐፍ በአንቀጽ በአንቀጽ የተከፋፈለ ሲሆን በገጽ ግን የተገለጸ ነገር የለው።ስለዚህ አንቀጽ 1-100=1፣አንቀጽ 1-100=2፣አንቀጽ 1-35=3 አንቀጽ ሁኖ የተከፈለ

ሲሆን ይህንን የሾተላይ የመድኃኒት መረጀ የምናገኘው ደግሞ አንቀጽ 1-100=2፣ ከአነቀጽ 59 ነው።ስለዚህ እንደ ሚከተለው በሰንጠረዥ መልክ ገለጻ ተከናውኖል።

የመጽሐፉ ዝርዝር መግለጫ		
ተራ ቁጥር	ዝርዝ	መግለጫ
1	መለያ	ርእስ፡መጽሐፈ መድሐኒት ወዕፀ ዳብዳቤ/ የመድኃኒት መጽሐፍ በአማርኛ/ የመጽሐፉ አይነት፣የብሪቲሽ የመድኃኒት መጽሐፍ ቋንቋ፣አማርኛ የማቴሪያሉ አይነት፣ብራና መጽሐፉ ጠባቂ ዳር እና ደር አንጨት ቀይ ቀለም ያለው የተጻሓፈው ጊዜ፣አይታወቅም ጽሕፈቱ ያለቀው ጊዜአታወቅም የመጽሐፉ ዕድሜ፣አይታወቅም መጽሐፉ ቅርፅ፣አራት ማዕዘን ሁኖ ሬክታንግል የቅጠሎች/folio/፣ገጹ ስላልተሰጠ ማወቅ አይቻልም አምድ፣3፡3 የእጅ ጽሐፍ፣በጥቁርእና በቀይ ቀለም የተጻፈ ሁኖ ጽሑፍን ለመለየት አስቸጋሪ ሐረግ፣አለው ስዕል፣አለው

		footnot/የግርጌ መግለጫ፣የለውም የልተጻፈ ገጽ አለው

2	የመጽሐፉ ይዘት	incipit/መግቢያ/ዛቲ መጽሐፈ መድሐኒት ዘወጽአት እም እየሩሳሌም --- "ይህ የመድኃኒት መጽሐፍ ከእየሩሳሌም የመጣ ነው---"በማለት ይጀምራል። Explicit/መደምደሚያ/ ደግሞ የአበተሬ ስር የዚህን ስር ደቁሰህ በስም ጠቅሰህ ሰፍተህ ያዝበ ማለትይጨርሳል።

ሠንጠረዥ 3፣መጽሐፈ መድሐኒት/የመድኃኒት መጽሐፍ ብሪቲሽ 828/አንቀጽ59/ ውጫዊና ውስጣዊ መግለጫ

መጠቃለያ ይህ መጽሐፈ መድሐኒት/ የመድኃኒት መጽሐፍ/የብራና መጽሐፍ ሲሆን የመጽሐፉ መለያቁጥር Birutish(ብሩቲሽ)828 ነው። ቀኑን እና ዓመተ ምሕረቱን ግን አይናገርም፡፡ ከመጽሐፉ ከፊደል አጣጣል በመነሣት Period vi-The Räqiq Script (mid17th-mid19th.AD) የረቂቅ ጽሑፍ 17ኛ እና 19ኛ ክፍለ ዘመን የተጻፈ መኾኑን ያመለክታል፡፡የተጻፈው በአማርኛ ቋንቋ ሲሆን መጽፉን የጻፈውን ሰው ወይም ደራሲ ይህ ነው ብሎ አይነገርም።የተጻፈው ጊዜና ያለቀውን ጊዜም አይታወቅም።ሽፋኑን ስንመለከት በእንጨት ገበታ የተጠረዘ ቀይ ቀለም ያለው ሲሆን ከጽሑፉ ከመድረሱ በፊት ለመከላከያነት የተቀመጡ ኹለት ቅጠሎች ያልተጻፈባቸዉ ከጽሑፉ በፊትይገኙበታል፡፡ አምድን በተመለከተ ሦስት አምድ ያለው ሲኾን የተጻፈበት ቋንቋ ደግሞ በዋነኝነት

አሜርኛ ነው።እንዲሁም የተዘጋጀበት ማቴሪያልን በተመለከተ ቆዳ ሲኾን የምን እንስሳ ቆዳ እንደኾነ ግን ለይቶ ማወቅ አይቻልም፡፡የመጽሐፉቅርጽ አራት ማዕዘን ሲሆን የብራናውን ክብደት እና እርዝመት በወርድ እና በቁመት ለመለካት እኔ የተጠቀምኩት በበይነመረብ (BnF) የወረደውን መጽሐፍ (ሶፍት ኮፒ) በመኾኑ መለካት ባለመቻሌ ይህ ነው ለማለት አይቻልም፡፡

በመቀጠልም ጸሐፊውን በተመለከተ መጽሐፈ መድኃኒት ወዕፀ ዳብዳቤ ማን እንደጻፈው አይገልጽም፡፡አጀማመሩን ስንመለከት ከየት ቦታ አንደተጻፈ በመግለጽ ይጀምራ።ዛቲ መጽሐፈ መድኃኒት ዘወጽአት እም እየሩሳሌም በማለት ሲጀምር፤ አጨራረሱ ደግሞ የአበተሬ ስር የዚህን ስር ደቁሰህ በስም ጠቅሰህ ሰፍተህ ያዝ በማለት ይጨርሳል። ሐረግ አለው።ፎሊዮ ግን የለውም።

3.8.3 ዕፀ ዳብዳቤ

ይህ ዕፀ ዳብዳቤ መጽሐፍ የሚጀምረው ከገጽ 173 በመሆኑ የመጽሐፉን ቁጥር ወይም ኮድ፣አጀማመር፣በአጠቃላይ የመጽሐፉን ውጫዊ ገጽታን ለመስጠት አልተቻለም።



ፎቶ ግራፍ 3፣ዕፀ ዳብዳቤ

የመጽሐፉ ዝርዝር መግለጫ		
ተራ ቁጥር	ዝርዝር	መግለጫ
1	ገለጻ	ቋንቋ፣አማርኛ ማቴሪያል፣ወረቀት አምድ፣አንድ የእጅ ጽሕፈት፣ደማቅ ጥቁርና ቀይ ቀለም footnot/ፉት ኖት የለም ሐረግ፣አለው የገጽብዛት፣733-752 ባዶ ወረቀት፣የለም
2	የመጽሐፉ አጀማመርና መዝጊያ	incipit/አጀማመር/፣ከመሃል ስለጀመረ የለም Explicit/መዝጊያ/፣አይታወቅም

፡ሠንጠረዥ 4 የዕፀ ዳብዳቤ ውስጣዊ መግለጫ

ማጠቃለያ የመጽሐፍ አይነት ወረቀት ሲሆን ቋንቋውም አማርኛ ነው።በእጅ የተጻፈ እና ባለ አንድ አምድ ደማቅ ሁኖ በጥቁር እና በቀይ ቀለም የተጻፈ ነው።ፉት ኖት፣የሌላው ሲሆን ሐረግ ግን አለው።ስለዚህ የዚህ ዕፀ ዳብዳቤ መጽሐፍ ከግማሽ ገጽ ስለሚጀምር ሙሉ በሙሉ መረጃውን አለገኘሁም።

3.8.4 መጽሐፈአድኅኖት




- ስለ ሾተላይ

1ኛ/ የሙጨሙላ ሥጋና ጉበት፡ የእስሰት ሥጋ፡ የዘርሙ እንቧይ ስር፡
ባት ቦታ ነቅለህ በእንድ ላይ ውቅጠ በጂበራ ውሃት ለውሰ ለህፃኑና
ናቱም አሰፍተው እንዲይዙት ማድረግ ነው፡

2ኛ/ የማርያም መቀነት፡ የግዜዋ፡ የደባቁር፡ የእበተሬ፡ የድግንድግ፡
ራቸውን የለመሊና የጥንጁት ተቀጽላቸውን ውቅጠ በነሙ ማር ለውሰ ጽንሱ
ረበት ጀምሮ በየሳምንቱ ወይም በየሁለት ሳምንት ግማሽ ማንኪያ ማዋጥ
፡

ፎቶ ግራፍ 4፣የመጽሐፈ አድኅኖት መጽሐፍ(2010 ገጽ102 የተወሰደ

የመጽሐፉ ውጫዊና ውሰታዊ መግለጫ

የመጽሐፉ ዝርዝር መግለጫ		
ተራ ቁጥር	ዝርዝር	መግለጫ
1	የመጽሐፉ ውጫዊ መግለጫ	የመጽሐፉ ርእስ መጽሐፈ አድኅኖት የመጽሐፉ ጸሐፊ መሪራስ አማን በለይ የመጽሐፉ አይነት ጥቅሙ ሙሉ ጤና ለሁሉ ዓመተ ምሕረት 20006 የመጽሐፉ ሽፋን በወፍራም ወረቀት ቅርፁ ሬክታንግል የመጽሐፉ ክብደት አልተገለጸም የመጽሐፉ ርዝመት አልተለካም
2	ውስታዊ ገጽታ	ማቴሪያሉ ወረቀት አምድ ባለ አንድ folio(ፎሊዮ) 169 የመስመሩ ብዛት ከ25-27

		ከአንድ መስመር የተጻፉ የቃላት ብዛት ከ8-10
3	3 Paleographical Feature (የፊዳለት	የመጽሐፉ ጽሑፍአማርኛአንዳንዴም ግእዝ ጽሕፈት በደማቅ መልክ በእጅ የተጻፈ ቀለም ሙሉ በሙሉ ጥቁር የሥርዓተ ነጥብ ሁኔታ ሁለት ነጥብ መጨረሻ ላይ እና ነጠላ ሰረዝ፣ሁለት ነጥብ ከሰረዝ ሐረግ የለውም ማርጅናል ኖት የለውም
4	የመጽሐፉ መግቢያና መደምደሚያ	incipit(መግቢያ) በመቅድም እግዚአብሔርን በመመስገን እንዲህ በማለት ይጀምራል አንድ አምላክ ቸር አባት ጌታ የሆንከን እግዚአብሔር ሆይ በተቀደሰው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስምህ----።ሲጀምር Explicit(መደምደሚ)አግዚአብሔርን በመመስገን እንዲህ በማለትይጨርሳል የተወደደና የተከበረ ምስጋና ለአንተ ይገባሃል ስምህን ለማመስገን ያብቃንአንተን እንደገና ለዘላለሙ ስምህን ለመባረክና ለመቀደስ ያብቃን አንተን ብቻ ተመምነናል ንጹህ ህሊናፍጠርል ይፍጠርል አሜን ይሁንልን።

ሠንጠረዥ 5፣የመጽሐፉ አድጎኖት (2010)መጽሐፉ ውጫዊና ውሰታዊ መግለጫ

ማጠቃለያ መጽፉመጽሐፉ አድጎኖት ጥቅሙ ሙሉ ጤና ለሁሉ የሚል ሲሆን በ2006 ዓ/ም በመሪራስ አማን በላይ የተጻፈ ነው።።ቅረጽ አራት ማዕዘን ሁኖ ሬክታንግል ሲሆን ጽሑፉ የተጀመረበት ቀን ግን አይታወቅም።።ጽሑፉ የተጠነቀቀበት ዓመተ ምሕረት 2006 ሲሆን የተጻፈውም ቋንቋ ደግሞ በአማርኛ ነው።በአጠቃላይ 339 ገጾች አሉት።።በጽሕፈቱ ላይ ጥቁር ቀለም ብቻ ተጠቅሞል።።በመጨረሻም ሁለት ነጥብ እና እንደ እስፈላጊነቱ ነጠላ ሰረዝ ነጥብ ተጠቅሞል።።ባለ አንድ አምድ ነው።።ማቴሪያሉ ወረቀት ሲሆን (folio)የግርጌ መግለጫ እና ሐረግ የለውም።።incipit(መግቢያ)በመቅድም እግዚአብሔርን በመመስገን እንዲህ በማለት ይጀምራል አንድ አምላክ ቸር አባት ጌታ የሆንከን እግዚአብሔር ሆይ

በተቀደሰው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስምህ----።ብሎ ሲጀምር መዝጊያው በምርቃት እንዲህ በማለት ይጨርሳል፡፡የተወደደና ተከበረ ም ስጋና ለአንተ ይገባሃል ስምህን ለማመስገን ያብቃን አንተን እንደገና ለዘላለሙ ስምህን ለመባረክ ለመቀደስ ያብቃን አንተን ብቻ ተመምነናል ንጹህህሊና ፍጠርልን ይፍጠርልን አሜን ይሁንልን።

3.8.5.መጽሐፈ ፈውስ



ፎቶ ግራፍ 5፣መጽሐፈ ፈውስ/የድህነትመጽሐፍ/ETHIOPIEN 402 GURIAULE 98/መጽሐፍ

መግለጫ		
ተራ ቁጥር	የመጽሐፉ ገለጻ	የመጽሐፉ ርእስ፣የግእዝ የመድኃኒት መጽሐፍ የተጻፈበት ቋንቋ፣ግእዝ እና አማርኛ ማቴሪያል ብራና በእንስሳት ቀዳ የተሠራ የመጽሐፉ ሽፋን፣የእንጨት ሁኖ ቀይ ቀለም የተቀባ ቅርፅ አራት ማዕዘን ሁኖ ሬክታንግል folio(ፎሊዮ) 94 ከጠባቂ ቅጠሎች ጋር አምድ ከ1-2 አጅ ጽሑፍ፣በጥቁር እና በቀይ ቀለም የተጻፈ ሐረግ የለውም መጨረሻ ላይ ኖት የለውም

2	የመጽሐፉ ይዘት	incipit(መግቢያ) ፡ወለከ ንፈኑ አኮቴት በስመ አብ ወወልድወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ንዌጥን ዘንተ መጽሐፈፈውስ ሥርአ[ዓ]ት ዘወጽአ እመንበረ ማርቆስ...፡፡ ጸሐፊ አኤርሚያስ ነቢይ የመስመር ሁኔታከ25-27 በየገጹ የተገኘው ከኢትዮጵያ በለቤቱ የማይታወቅ የሥርዓተ ነጥብ ሁኔታ፣አራት ነጥብ ሁለት ነጥብ፣---- Explicit; አምላከ ፋኑኤል እቀበኒ ወአድነኒ እመከራ ሥጋወነፍስ ሊተ ለግብርከ፡፡እ፡፡

፡ሠንጠረዥ6፣የመጽሐፈ ፈውስ/ መድህነት መጽሐፍ/ETHIOPIEN 402 GURIAULE 98/ ውጫዊና ውስጣዊ መግለጫ

መጠቃለያ ይህ መጽሐፈ ፈውስ የግእዝ የብራና የህክምና ጽሑፍ ነው፡፡ የተጻፈውም በአማርኛ እና በግእዝ ቋንቋ ነው፡፡ሽፋኑን ስንመለከት ብራና፣ከእንጨት የተሰራ፣ሽፋንና ቀይ ቀለም ያለው፡፡መጠኑ ያልታወቀ አራት ማእዘን ያለው፣ፎሊዮ94 የጥበቃ ቅጠሎችን ጨምሮ፡፡ጸሐፊው ስም ኤርሚያስ ነቢየ፡፡ዘመን/century/ 20፡፡ሲሆን ጽሑፉ የተጀመረበት ዓመተ ምሕረት ግን አይታወቅም፡፡አምዶች ከአንድ እስከ ሁለት ሲሆን፡የእጅ ጽሑፍ በጣም በጥሩ ሁኔታ ጎላ በማለት በጥቁርና በቀይ ቀለም ተጽፎል፡፡ ጸሐፊው በመጨረሻ ላይ ሙሉ ማቆሚያዎች እና ነጥቦችን ተጠቅሞል፡፡በተጨማሪም ከቆዳ የተዘጋጀ ብራና

ነው፡፡ነገር ግን የምን ቆዳ እንደ ሆነ ግን አይገልፅም በእየገጹ ከ24-27 መስመሮች አለት፡፡እያንዳንዱ መስመር በአማካይ እስከ ሶስት ቃላትን ይዞል፡፡እያንዳንዱ ቃል ከሁለት እስከ ስድስት ፊዳላትን ሊይዙ ይችላሉ፡፡ሐረግ እና ፡ኮሎፎን ኖት የለውም፡፡

መግቢያ/ Incipit:/ ወለከ ንፈኑ አኩቴት በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፀ አምላክ ንዌጥን ዘንተ መጽሐፈ መድኃኒት፡፡

መዝጊያ/Explicit / አምላክ ፋኑኤል እቀበኒ አድነኒ እመከራ ሥጋ ወነፍስ ሊተ ለገብርከ፡፡እ፡፡

3.9.የምርምር ሥነ ምግባር

